የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

# በሀገር ውስጥ በሴቶችና በሕፃናት የመነገድ ድርጊት የባለግዴታዎች ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ የተደረገ የክትትል ሪፖርት



Photo credit: Ermias Dejene (EHRC 3rd Annual Human Rights Film Festival photography competition submission)

www.ehrc.org

ታኅሣሥ 2016 ዓ.ም.

# ማውጫ


የምሕጻረ ቃላት እና የእንግሊዘኛ ቃላት ፍቺ ...... 1

አንኳር ጉዳዮች ...... 1

ክፍል አንድ ...... 6

1. መግቢያ ...... 6

2. የክትትሉ ዓላማ ...... 7

3. የመረጃ አሰባሰብ ሥነ ዘዴ ...... 7

4. የክትትሉ ውስንነቶች ...... 9

ክፍል ሁለት ...... 10

2. አግባብነት ያላቸው የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች ...... 10

2.1. ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ...... 10
2.2. በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ተፈጻሚነት ያላቸው ዓለም አቀፍ መመዘኛዎች ...... 12
2.2.1. በሰዎች የመነገድ ድርጊትን በብሔራዊ ሕግጋት ወንጀል ማድረግን ጨምሮ ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ ...... 13
2.2.2. ለተጎጂዎች ድጋፍ እና የጥበቃ እርምጃዎችን የማመቻቸት ግዴታ ...... 14
2.2.3. የወንጀል ምርመራ በማድረግ የአጥፊዎችን ተጠያቂነት የማረጋገጥ ግዴታ ...... 14
2.2.4. የትብብር ማዕቀፍ የመዘርጋት ግዴታ ...... 14
2.3. በሰዎች የመነገድ ድርጊትን የተመለከቱ የኢትዮጵያ የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች ...... 15

ክፍል ሦስት ...... 17

3. ዋና ዋና ግኝቶች ...... 17

3.1. በሰው መነገድ ወንጀል ተጎጂዎች እና የደረሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ...... 17
3.2. በሀገር ውስጥ የሚደረግ በሴቶችና በሕፃናት የመነገድ ድርጊት የባለግዴታዎች ምላሽ አሰጣጥን የተመለከቱ ዋና ዋና ግኝቶች ...... 19
3.2.1. በሰዎች የመነገድ ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችሉ የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች ...... 19
3.2.2. የጥናትና ምርምር ሥራዎች ...... 20
3.2.3. የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የትምህርት ተደራሽነት እና ግንዛቤ ማሳደግ ሥራዎች ...... 21
3.3. በወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የተወሰዱ እርምጃዎች ...... 22
3.3.1. ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የፖሊስ እና የዐቃቤ ሕግ ተቋማዊ አሠራር ...... 22
3.3.2. የወንጀል ምርመራ እና ክስ አቀራረብ ...... 22
3.3.3. የሕግ አስከባሪ አካላትን ዐቅም ለማጎልበት የተወሰዱ እርምጃዎች ...... 23
3.3.4. የሀገር ውስጥ በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን የተመለከተ የመረጃ ሥርዓት ...... 23
3.4. የተጎጂዎች ጥበቃ እና መልሶ ማቋቋም ሥራዎች ...... 24
3.5. በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን በተመለከተ የትብብር ሥርዓትን መፍጠር ...... 25

ክፍል አራት ...... 27

4. ምክረ ሐሳብ ...... 27

## የምሕጻረ ቃላት እና የእንግሊዘኛ ቃላት ፍቺ

| | |
|---|---|
| ዓ.ም. | ዓመተ ምሕረት |
| እ.ኤ.አ. | እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር |
| ኢሰመኮ | የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን |
| ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. | የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ |
| ተ.መ.ድ. | የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት |
| ILO | International Labour Organization (ዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት) |
| CEDAW | Convention on the Elimination of All forms of Discrimination against Women (በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት) |
| CRC | Convention on the Rights of the Child (የሕፃናት መብቶች ስምምነት) |
| Palermo Protocol | The Protocol to Prevent, Suppress and Punish Trafficking in Person Especially Women and Children (በሰው በተለይም በሴቶች እና ሕፃናት የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለማስቀጣት የወጣ ፕሮቶኮል) |
| UNTOC | የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስምምነት (The UN Convention against Transnational Organized Crime) |
| ILC82 | The ILO Convention No 182 on the Elimination of All Form of Child Labor |

## አንኳር ጉዳዮች

በሰዎች የመነገድ ድርጊት በሰዎች ሕይወት፣ አካል፣ ደኅንነትና ክብር ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ፣ የሰዎችን መብቶችን እና ነጻነቶችን የሚያግድ ወይም ሙሉ በሙሉ እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ ነው:: ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች ሴቶች እና ሕፃናት በሰው የመነገድ ወንጀል ያላቸውን ከፍተኛ ተጋላጭነት ታሳቢ በማድረግ ልዩ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው ይደነግጋሉ::[1]

በሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ድርጊት መነሻ፣ መተላለፊያና መዳረሻ ተብለው በተለዩ ቦታዎች ኮሚሽኑ በሁለት ዙር ክትትል አካሂዷል:: በመጀመሪያው ዙር በሁለት የክትትል ቡድን ከየካቲት 22 እስከ ጥር 1 ቀን 2015 ዓ.ም. በአማራ ክልል፤ በባሕር ዳር ከተማ እንዲሁም በአፋር ክልል፤ በሰመራና ሎጊያ ከተሞች ክትትል ተደርጓል:: በሁለተኛው ዙር በአራት የክትትል ቡድን በኦሮሚያ ክልል በምሥራቅ ሸዋ ዞን፤ በአዳማ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የኦሮሚያ ክልል ቢሮዎች፣ በቀድሞ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በአሁኑ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በወላይታ ዞን፣ በሲዳማ ክልል ሃዋሳ ከተማ በሚገኙ ተቋማት እንዲሁም በአዲስ አበባ የፌዴራል ተቋማት ከመጋቢት 10 እስከ 15 ቀን 2015 ዓ.ም. ክትትል ተደርጓል :: በክትትሉ 23 የክልል ቢሮዎች፣ 6 የፌዴራል ተቋማት፣ 4 ከተማ አስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች፣ 14 የዞን መምሪያዎች እና የፖሊስ ጣቢያዎች፣ 13 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ 4 የሥራ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች፣ 21 ተጎጂዎች እና የተጎጂዎችን ታሪኮች የተመለከቱ ሰነዶች ታይተዋል::

በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ በሰዎች የመነገድ ድርጊት በሀገር ውስጥ የሚፈጸም ወይም ድንበር ተሻጋሪ ሊሆን ይችላል:: ይህ ክትትል በሀገር ውስጥ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚደረግን በሰዎች የመነገድ ድርጊት በተመለከተ የባለግዴታዎች ምላሽ አሰጣጥን ከሰብአዊ መብቶች መርሖዎች እና መመዘኛዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን በመመዘን አንኳር ግኝቶችን እና ምክረ ሐሳቦች የሚያቀርብ ነው::

***በክትትሉ በሴቶች እና በሕፃናት የመነገድ ድርጊት ምክንያት መድረሳቸው የተረጋገጡ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች:*** ከተጎጂዎች ማቆያ፣ ከክልል የሴቶች እና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮዎች እንዲሁም ለተጎጂዎች በተደረገ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ሴቶች እና ሕፃናት በሰው በመነገድ ድርጊት ሳቢያ ከጾታዊ እና አካላዊ ጥቃት የመጠበቅ፣ ከአድልዎና መገለል የመጠበቅ መብት፣ የአካልና የአእምሮ ደኅንነት መብት፣ የነጻነትና ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት፤ ፍትሕ የማግኘት መብቶቻቸው እንደተጣሱ ያስረዳል:: በተለይም ሕፃናት በሰው የመነገድ ድርጊት ተጎጂ በመሆናቸው ከወላጆች እንክብካቤና ጥበቃ የማግኘት መብት፣ የትምህርትና ጤና እንዲሁም ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን የማግኘት መብቶቻቸውን አጥተዋል:: ተጎጂዎች ትምህርት እና የተሻለ ሕይወት እንደሚኖራቸው ቃል ተገብቶላቸው በዘመድ፣ በደላላ ወይም በሌሎች ታግዘው ወደ ከተማ በመምጣት ለድብደባ፣ ጾታን መሠረት ላደረጉ ጥቃቶች፣ ለጉልበት ብዝበዛ እና የግዳጅ ሥራ እንዲሁም ለኢ-ሰብአዊ አያያዝ እንደሚጋለጡ ለማረጋገጥ ተችሏል:: ተጎጂዎች እነዚህ መሠረታዊ መብቶች ላይ ተደራራቢና ዘርፈ ብዙ የመብት ጥሰት ቢፈጸምባቸውም በየደረጃው

[1] UNDOC; Legislative Guide for the Protocol to Prevention, Suppress and Punish Trafficking in Persons, Especially Women and Children (2020) P.6.

ኃላፊነት የተጣለባቸው አካላት ጉዳያቸውን መርምረው እና ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃዎች ወስደው የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ማረጋገጥ እና ተጎጂዎችም ካሳን ጨምሮ ውጤታማ መፍትሔ እንዲያገኙ ባለማስቻላቸው ፍትሕ የማግኘት መብታቸው ላይም ጥሰት መኖሩን ያሳያል፡፡

***የመረጃ አያያዝ ውስንነት፡*** በሰው የመነገድ ድርጊት ተጋላጭ ወይም ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶቻቸው ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ፣ እንዲጠበቁ እና እንዲሟሉ መንግሥት የተደራጀ፣ ትክክለኛ፣ የተሰባጠረ፣ ለአጠቃቀም ምቹ፣ ለማኅበረሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ የሆነ የሰብአዊ መብቶች መረጃ እና የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚህ አግባብ ክትትል በተደረገባቸው ቦታዎች፣ በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን የተመለከቱ መረጃዎች፣ የመብት ጥሰቶች ወይም ወንጀሎች በዐይነትና መጠን፣ እንዲሁም ጠቅላላ በፍትሕ ሂደት ያሉትን ገጽታዎች በሚያሳይ መልኩ የተሰባጠረና የተደራጀ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የተገኙ መረጃዎችም በተለያዩ ተቋማት መለያየታቸውን፣ መረጃ በሚደራጅበት ጊዜ ክስ በተመሰረተባቸው ወንጀሎች ተዘርዝሮ አለመቀመጡን፤ በጥቅሉ በሀገር ውስጥ የሚደረጉ በሰዎች በተለይም በሴቶችና በሕፃናት የመነገድ ድርጊትን አስመልክቶ መረጃ ለማግኘት አመቺ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

***በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን የመከላከል ሥራዎች አናሳ መሆን፡*** ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወጡ ስምምነቶች መሠረት መንግሥታት በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን ለመከላከል ሁሉን አቀፍ ሕጋዊ፣ ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ እና ማኅበራዊ ስልቶች መንደፍ አለባቸው፡፡ እነዚህ ስልቶች መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር፣ የድርጊቶቹ መንስዔዎች፣ ባሕርያት፣ ክብደት እና ውጤቶችን የተመለከቱ ጥናቶችን በማከናወን መረጃን መሠረት ያደረጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታዎች ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ረገድ የክትትል ግኝቱ የሚያሳየው በሰው መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጡ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች እንዲሁም የድርጊት መርኃ ግብሮች ከሁሉን አቀፍ ምላሽ ይልቅ፤ በዋናነት ሰውን በሕገ ወጥ ድንበር ማሻገር እና ከሀገር ውጪ በሰው የመነገድ ድርጊት ላይ ብቻ ትኩረት ያደረጉ መሆናቸውን ነው፡፡ በሰው መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በብሔራዊ ደረጃ የተቋቋመው ብሔራዊ የትብብር ጥምረት ሪፖርቶች፣ የሥራ ዕቅዶች እና ጥናቶችም በዋናነት የትኩረት አቅጣጫቸው ድንበር ማሻገር እና ከሀገር ውጪ በሰው መነገድ ድርጊቶች ላይ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በወላይታ ዞን ከተሠራ አንድ ጥናት እና በከፍተኛ ተቋማት ከተሠሩ ጥናቶች በስተቀር በሀገር ውስጥ በሴቶች እና በሕፃናት መነገድ፣ ባሕርያት፣ መንስዔዎች ክብደት እና ውጤቶች በጥናትና ምርምር በአግባቡ አልተለዩም፡፡

በሰው የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የተደራጀ መዋቅር ከመፍጠር አንጻር በፌደራል ደረጃ ብሔራዊ ምክር ቤት እና የትብብር ጥምረት የተቋቋሙ ቢሆንም የተወሰኑ ክልሎች ብቻ ጥምረቱን ባለማቋቋማቸው እና በጀት የሌላቸው መሆኑ በሀገር ውስጥ የሚደረጉ የሰዎች የመነገድ ድርጊቶችን እና እሱን ተከትሎ የሚከሰቱ ዘርፈ ብዙ የመብት ጥሰቶችን ለመከላከል መንግሥት የሚወስዳቸው እርምጃዎች በቂ አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡

መንግሥት በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን ለመከላከል መነሻና ሳቢ ምክንያቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ፣ ለማኅበረሰቡ፣ ለሕግ አስከባሪ አካላት እና ቁልፍ ኃላፊነት ላይ ላሉ ሰዎች ግንዛቤ የማሳደግ ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም የሥራ ዕድል ፈጠራና የብድር

አማራጮች በዋናነት ከአረብ ሀገር ተመላሾች ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ፣ በሀገር ውስጥ በሰው ለመነገድ ድርጊት መነሻ በሆኑ ቦታዎች ከተወሰዱ መጠነኛ እርምጃዎች በስተቀር በተቀናጀ መልኩ መነሻ ምክንያቶችን ለመቀነስ የትምህርት እና የሥራ ዕድሎች አነስተኛ ናቸው፡፡

ክትትል የተደረገባቸው የክልል ቢሮዎች እና ሕግ አስፈጻሚ አካላት በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን ለመከላከል የሚያስችል በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸው፣ ቢሮዎቹ የተሰጣቸው ኃላፊነት ግልጽ አለመሆን፣ የበጀት እጥረት እንዲሁም የመከላከል ሥራዎችን በትብብር የመሥራት ችግሮች እንዳሉ ታይቷል፡፡ መንግሥት ድርጊቱን ለመከላከል የተቀናጀ፣ ቀጣይነት ያለው እና ሊመዘን የሚችል ለሕዝቡ በተለይም ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ማሳደግ ቢኖርበትም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ከሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በስተቀር በሀገር ውስጥ መነገድ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የግንዛቤ ማስጨበጫና የሥልጠና መርኃ ግብሮችን ለማግኘት አልተቻለም፡፡ እነዚህ ግኝቶች በጠቅላላው በፌዴራል መንግሥት እና የክልል መንግሥታት በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል ተገቢውን ትኩረት እንዳልተሰጠው ያሳያሉ፡፡

***በሀገር ውስጥ በሰው የመነገድ ድርጊት ለተጎጂዎች የሚደረጉ የጥበቃ እና የመልሶ ማቋቋም ሥራዎች ሰብአዊ መብቶችን ማእከል ያደረጉ አለመሆን:*** በክትትሉ የፍልሰት ተጎጂዎች ብሔራዊ ቅብብሎሽ ሥርዓት ረቂቅ መመርያ መኖር፣ ክትትል በተደረገባቸው ቦታዎች የተጎጂዎች ጊዜያዊ አገልግሎት መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት እንደሚሰጥና እነዚህም ተቋማት ከመንግሥት ጋር የቅብብሎሽ ሥርዓት እንዳላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በእነዚህ ማእከላት የሥነልቦና፣ የጤና፣ የምግብ፣ ነጻ የሕግ ምክር አገልግሎቶችና የሕይወት ክህሎት ስልጠና እንደሚሰጡ ለማየት ተችሏል፡፡ ሆኖም የተጎጂዎች ጥበቃና ድጋፍ ፕሮግራሞች በዋናነት ከውጭ ሀገር ተመላሾች ላይ ብቻ ያተኮሩ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ተጎጂዎችን ወደ ቤተሰብ መልሶ ለመቀላቀል የሚሰጡ ኢኮኖሚያዊ ድጋፎች፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የቴክኒክ ክህሎትና የንግድ ሥራ አመራር ሥልጠናዎች ከውጭ ሀገር ተመላሾች ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በተወሰነ ደረጃ የሚሰጡትም የገንዘብ ድጋፎች በጥናት ላይ ያልተመሠረቱ በመሆናቸው በሰው የመነገድን ዑደትን የማያስቀጥል ዕድል ያለው መሆኑ ታይቷል፡፡ ለምሳሌ ተጎጂዎችን ለማቋቋም የሚሰጡ የገንዘብ ድጋፎችን ተጎጂዎች ወደ አካባቢያቸው ይዘው ሲመለሱ ሌሎች ይህን ድጋፍ ለማግኘት መፍለስን ወይም በሰው የመነገድ ድርጊት ተጋላጭና ተጎጂ መሆንን እንደ ዐይነተኛ አማራጭ እንደሚወስዱ ተገልጿል፡፡ በሌላ በኩል የተጎጂ ማእከላት በዋናነት በክልል ከተሞች የሚገኙ በመሆናቸው ተደራሽነታቸው ውስን ነው፡፡

**በሀገር ውስጥ በሰው የመነገድ ወንጀል ፈጻሚዎችን ለማስቀጣት የሚያስችል የተደራጀ ሥርዓት አለመኖር:** በሰው መነገድና ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገርን በሚመለከት በተሟላ መልኩ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አዋጅ ቁጥር 1178/2012 (በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 11/2013 እንደተሻሻለው) መውጣቱ በሰው ለመነገድ ተግባራዊ የሚደረጉ መንገዶችን፣ ዘዴዎችን እና የሚደረግበትን ዓላማ ወንጀል ማድረጉ አበረታች ነው፡፡ መንግሥት ይህን ድርጊት ፈጻሚዎችን ለመቅጣት የሚያስችል ሕግ ከማውጣት በተጓዳኝ ወንጀሉን ለመመርመር፣ ለመክሰስ እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ዐቅም መፍጠር ይኖርበታል፡፡ በዚህ ረገድ በሀገር ውስጥ የሰዎች መነገድ ድርጊት በስፋት መኖሩን የሚያመለክቱ የተለያዩ አቤቱታዎች ቢቀርቡም ወንጀሉን

ለመመርመር ልዩ ብቃት ያላቸው ፖሊሶችን በክልሎች አለማደራጀቱ፣ የምርመራ ሥራዎች በአብዛኛው ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ላይ ትኩረት ማድረጋቸው ለመረዳት ተችሏል። ምርመራ ሲደረግም በሰው የመነገድ ድርጊቱን እና በሂደቱ የተጣሱ የሰብአዊ መብቶችን ዘርዝሮ ከመመርመርና ከመክሰስ ይልቅ በአንዱ የጥቃት ዐይነት ብቻ ጠቅልሎ ምርመራ በማካሄድ ክስ እንደሚቀርብና እና ይህን ጉዳይ የሚመለከት አጠቃላይ የክስ ምጣኔም ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል። በተጨማሪም ለሕግ አስከባሪ አካላት የሚሰጡ ስልጠናዎች በቂ አለመሆን፣ ክትትል በተደረገባቸው የፖሊስ ጣቢያዎች እና መምሪያዎች የሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ወንጀልን የሚመለከቱ የተሟላ መረጃዎች አለመኖር፣ በየእርከኑ ያሉ መረጃዎችን መለያየትና የተደራጀ አለመሆኑን ኢሰመኮ ተገንዝቧል።

## ምክረ ሐሳቦች

1. መንግሥት ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው በሰዎች መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሕግ እና የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት የተቋማት ዕቅድ፣ ማስልጠኛ መመሪያዎች፣ የመከላከል ሥራዎች፣ በሰዎች የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል እና ለመቆጣጣር የወጡ መመሪያዎች እና አዋጆች በሀገር ውስጥ የሚደረጉ በሰዎች የመነገድ ድርጊትን በተለይም በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን የተመለከቱ ጉዳዮችን ለይተው የሚያስቀምጡ እና ምላሽ የሚሰጡ እንዲሆኑ እንዲያደርግ፤
2. ብሔራዊ ትብብር ጥምረቱ በሀገር ውስጥ በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን ለመከላከል የሚያስችሉ መረጃዎችን በማሰባሰብና፣ በማጠናቀር፣ የድርጊቶቹን መንስዔዎች፣ ባሕርያት፣ ክብደት እና ውጤቶች የተመለከቱ ጥናቶችን እንዲሠራ፤ የጥናት ውጤትን መሠረት በማድረግ መነሻ እና ሳቢ ምክንያቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፤
3. በክልሎች ያሉ የትብብር ጥምረት መዋቅሮች አስፈላጊው በጀት እንዲመደብላቸው እና በትብብር ሥራዎች ላይ ያሉ ክፍተቶችን ለማስወገድ በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 መሠረት የክልል ምክር ቤቶች አግባብነት ያላቸውን ተቋማት ያቀፈ እና ተጠሪነቱ ለክልሉ ፕሬዝዳንት የሆነ ምክር ቤት በሕግ እንዲያቋቁሙ፣
4. የፍትሕ ሚኒስቴር እና የፌዴራል ፖሊስ፣ ከክልል ፍትሕ ቢሮዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካለት ጋር በመቀናጀት የሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ድርጊቶች መነሻዎችን፤ መዳረሻዎችን የሚያስከትላቸውን የመብት ጥሰቶች በሚያሳይ መልኩ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር መረጃዎች ለትንታኔ፣ ለሕግ እና ለፖሊሲ ማሻሻያዎች ግብአት ሊሰጡ በሚችል መልኩ የመረጃ ሥርዓት እንዲዘረጉ፤
5. በሀገር ውስጥ በሚደረጉ በሰዎች የመነገድ ድርጊቶች ላይ ያሉ ዝቅተኛ ምርመራ እና የክስ አቀራረብ ላይ ማስተካከያ በማድረግ፤ የምርመራና የክስ አመሠራረቱ ድርጊቱን ተከትሎ በደረሱ ጥቃቶች ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን ከዋናው ድርጊት ጀምሮ ያሉትን እያንዳንዳቸውን የመብት ጥሰቶች መሠረት ያደረገ እንዲሆን፤
6. የፌደራል እና የክልል መንግሥታት ሕፃናት ወደ ከተሞች በመፍለስና በልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች በመሰማራት ለብዝበዛ የሚዳረጉበትን ሁኔታ ለመቀነስ የማኅበራዊ መከላከያ ፕሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊ እንዲያደርጉ፤

7. የፍትሕ አካላት በሀገር ውስጥ በሚደረጉ በሰዎች የመነገድ ድርጊቶች ላይ ምርመራ በማድረግ ክስ በመመስረትና አጥፊዎችን ተጠያቂ በማደረግ ተጎጂዎች ካሳን ጨምሮ ውጤታማ መፍትሔ እንዲያገኙ የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንዲወስዱ፣ እንዲሁም
8. የሲቪል ማኅበራት በሰው የመነገድ ድርጊት ተጎጂ ለሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች በተለይም ለሴቶችና ሕፃናት የመጠለያ፣ የሥነልቦና ድጋፍና አገልግሎት፣ የሕግ ምክር አገልግሎት እንዲሁም የሥራ ክህሎት ስልጠናን የመሳሰሉትን ጠቅላላ ድጋፍና አገልግሎት እንዲሰጡ ኮሚሽኑ ምክረ ሐሳቡን ያቀርባል።

# ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

በሰዎች የመነገድ ድርጊት በዓለም አቀፍ ደረጃ አሳሳቢ የሆነ ጉዳይ ሲሆን ሰዎችን ያለፍላጎታቸው ለመበዝበዝ በማሰብና በኀይል ወይም በማስፈራራት ወይም ሌሎች የማስገደጃ ዘዴዎችን በመጠቀም ከምልመላ ጀምሮ ማጓጓዝንና ማዟዟርን የሚያጠቃልል የሰዎችን መብቶችን እና ነጻነቶችን የሚያግድ ወይም ሙሉ በሙሉ እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ነው። በድርጊቱ ሴቶችና ሕፃናት ተጋለጭ ሲሆኑ በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ያሉ፤ በገጠር የሚኖሩ፣ ዘመናዊ ትምህርት ያላገኙ፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃይ ሴቶች እና ሕፃናት ይበልጥ ተጋላጭነታቸው ይጨምራል። የተባበሩት መንግሥታት የዕፅ እና የወንጀል ተቆጣጣሪ ጽሕፈት ቤት (United Nations Office on Drugs and Crime — UNODC) እ.ኤ.አ. በ2022 በሰው መነገድ እና ሰዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ዓለም አቀፍ ሁኔታን በሚያሳየው ሪፓርቱ ወንጀሉ ሰዎችን ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንደሚያጋልጥ፣ በአፍሪካ በተለይም ከሰሀራ በረሃ በታች የሚኖሩ ሴቶች እና ሕፃናት ይበልጥ ተጋላጭ እንደሆኑ፣ ጦርነት እና ግጭቶችም በሰው የመነገድ ድርጊት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥሩ ያመለክታል።[2] በሰዎች የመነገድ ወንጀል በሕገ ወጥ መንገድ በሀገር ውስጥ ወይም ድንበርን በማሻገር በሁለት መልክ ይፈጸማል።

በአፍሪካም በሰዎች የመነገድ ድርጊት ሴቶችንም ሆነ ወንዶችን ተጋላጭ የሚያደርግ ሲሆን በተለይም ሴቶችና ሕፃናት በድህነት፣ በዘመናዊ ትምህርት እጦት እንዲሁም ጾታዊ ጥቃትን በመሳሰሉት ምክንያቶች ይበልጥ ተጋላጭ ናቸው። በአብዛኛው ለግዳጅ ሥራ፣ ወሲባዊ ብዝበዛ እና ያለዕድሜ ጋብቻ ለመሳሰሉት ምክንያቶች ታስበው ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ ይስተዋላል።

ኢትዮጵያ በሰው የመነገድ እና  በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ለማሻገር መነሻ እና መሸጋገርያ ሀገር እንደሆነች የተለያዩ ጥናቶች የሚያሳዩ ሲሆን ግጭት ድርቅ እና የኢኮኖሚ አለመረጋጋት ዋነኛ መንስዔዎቹ ናቸው።[3] በኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ወንጀል በተደራጀ መልኩ የሚፈጸም መሆኑ፣ በተለይ በሴቶች እና በሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ፣ ወሲባዊ ጥቃት፣ ለገንዘብ ተብሎ የሚደረግ ጠለፋ (በጉዞ ወቅት እና በመዳረሻ ላይ)፣ ባርነት እንዲሁም የመተላለፊያና መዳረሻ ቦታዎች ለአደጋ የማጋለጥ ዕድላቸው የሰፋ በመሆኑ ኮሚሽኑ በጉዳዩ ላይ ለወራት ያክል የቆየ ክትትል አካሄዷል። ምንም እንኳን ወንጀሉ አሳሳቢ የመብት ጥሰቶችን ቢያስከትልም

[2] UNODC, Global Report on Trafficking In Person, 2022
[3] በብሔራዊ የትብብር ጥምረት የፍልሰት አስተዳደር የአምስት ዓመ ት ስትራቴጂክ ዕቅድ፤ (2013 – 2017 ዓ.ም.) ፣ ታኅሣሥ ወር 2013 ዓ.ም.

በመንግሥት ወንጀሉን ለመግታት የተወሰዱ ሕጋዊ እና ተቋማዊ እርምጃዎች በአብዛኛው ሰዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ላይ ያተኮረ ነው።[4]

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) በሰው የመነገድ ድርጊት ሂደት ብዙ ቦታዎችን የሚሸፍን እንዲሁም በርካታ ሴቶችና ሕፃናት በዚህ ድርጊት ምክንያት መሠረታዊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶቻቸው የሚነኩ መሆኑን በመገንዘብ፤ የኮሚሽኑ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በየክልላቸው ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ እና የድርጊቱን ጥልቀት የሚያሳይ ዳሰሳ እንዲሠሩ ተደርጎ ውጤቱ በሀገር ውስጥ በተፈጥሮአዊ እና በሰው ሠራሽ ምክንያቶች የተከሰቱ መፈናቀሎች እና የኢኮኖሚ መቃወሶች ሴቶች እና ሕፃናትን ለማዘዋወር አባባሽ ምክንያቶች መሆናቸው እና በሁሉም ክልሎች በሚባል ሁኔታ በሰው መነገድ በተለይም ሕፃናት እና ሴቶች ተጋላጭ እንደሆኑ አመላክቷል። ኮሚሽኑ በመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም. የመንግሥት አስፈጻሚዎች፣ ባለድርሻ አካላት እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ባዘጋጀው ምክክር በሀገር ውስጥ በሰዎች መነገድ ድርጊት ተገቢውን ትኩረት አለማግኘቱንና የሚሠሩ ሥራዎች ሰብዓዊ መብቶችን ማእከል ያደረጉ አለመሆኑ ተነስቷል። በተጨማሪም በሕፃናት መነገድን በተለመለከተ ኮሚሽኑ ተደጋጋሚ ጥቆማዎች እየደረሱት በመሆኑ ይህን ክትትል ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 2. የክትትሉ ዓላማ

የዚህ ክትትል ዓላማ  በሴቶች እና በሕፃናት የመነገድ ድርጊት መነሻ፣ መተላለፊያና እና መዳረሻ ተብለው በተለዩ አካባቢዎች የባለግዴታዎች ምላሽ አሰጣጥ ላይ የሰብአዊ መብቶች ክትትል ማከናወን ነው።

## 3. የመረጃ አሰባሰብ ሥነ ዘዴ

ክትትሉ የተከናወነው በሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ወንጀል ሂደት ውስጥ፣ በተለይም የተጎጂዎች መነሻ፣ መተላለፍያ እና መዳረሻ ተብለው የተለዩ ቦታዎችን በማካተት እና ከዚህ ቀደም በተለያዩ ዓለም አቀፍ እና ሀገራዊ ተቋማት የተሠሩ ጥናቶችን፣ ለኮሚሽኑ የደረሱ ጥቆማዎችን፣ በሰዎች መነገድን አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር ግንቦት 11 ቀን 2015 ዓ.ም. የተካሄደውን  የውይይት መድረክ እንዲሁም የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት የሚገኝባቸው የክልል ከተሞች የተደረጉ ክትትሎችን መሠረት በማድረግ ነው። በዚህም መሠረት በሰው የመነገድ ድርጊት በብዛት የሚከሰትባቸው ቦታዎች በክትትሉ የተሸፈኑ ሲሆን እነዚህም  አዲስ አበባ፣

---

[4] በብሔራዊ የትብብር ጥምረት የፍልሰት አስተዳደር የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (2013 — 2017 ዓ.ም.)፣ ታኅሣሥ ወር 2013 ዓ.ም. ፣ 2022 Trafficking in Persons Report: Ethiopia; https://www.state.gov/reports/2022-trafficking-in-persons-report/ethiopia/

አዳማ፣ በወላይታ ዞን፣ በባሕር ዳር፣ እንዲሁም ሰመራና ሎጊያ ከተሞች ናቸው። የክትትል ቡድኑ 23 የክልል መንግሥት ቢሮዎች፣ 6 የፌደራል መንግሥት ተቋማት፣ 4 ከተማ አስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች፣ 14 የዞን መምሪያዎች እና የፖሊስ ጣቢያዎች፣ 13 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ 4 የሀገር ውስጥ የሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎችን በማነጋገርና ሰነዶችን በመመርመር፣ እንዲሁም 21 የወንጀሉ ተጎጂዎችን ቃለመጠይቅ በማደረግ እና የተጎጅ ታሪኮችን የተመለከቱ ሰነዶች በመመልከት መረጃዎች ተሰብስበዋል።

በተጨማሪም ከባለግዴታ ተቋማት ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ቃለ መጠይቆች፣ የተቋማት የዕቅድ እና ሪፖርት ምዘና፣ ውሳኔ ያገኙ መዛግብት ምልከታ፣ በፖሊስ ጣቢያዎች እና የተጎጂ ማቆያ ማዕከላት ምልከታ ተካሂዷል።

| ተ.ቁ. | መረጃ የሰጡ አካላት | መረጃ የተሰበሰበበት ዘዴ |
|---|---|---|
| 1 | በፌደራል የመንግሥት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች | ከ13 ቁልፍ መረጃ ሰጪ የሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎችን ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። |
| 2 | በአዲስ አበባ የሚገኙ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ማቆያ ማእከላት | ከ 9 ባለሙያዎች እና እንዲሁም አንድ ኃላፊ ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። በሀገር ውስጥ የሚደረግ በሰዎች በመነገድ ድርጊት 2 ውሳኔ የተሰጠባቸው መዝገቦች ታይተዋል። |
| 3 | በአማራ ክልል ባሕር ዳር ከተማ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች | ከ 4 የሥራ ኃላፊዎች እና 6 ባለሙያዎች ጋር ቃለመጠይቅ ተደርጓል። |
| 4 | በባሕር ዳር ከተማ የሚገኙ የአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች | ከ 4 የአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ተጠቃሚ ግለሰቦች እና 2 ባለቤቶች ጋር ቃለመጠይቅ ተደርጓል። |
| 5 | በባሕር ዳር ከተማ የሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ እና የተጎጂዎች ማእከል | በፖሊስ ጣቢያው እና የተጎጂዎች ማእከል ምልከታ ተደርጓል።<br><br>ከ 4 ተጎጂዎች ቃለመጠይቅ ተደርጓል። |
| 6 | በቀድሞ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በአሁኑ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን እና በሲዳማ ክልል ሃዋሳ ከተማ | ከ 20 ቁልፍ መረጃ ሰጪ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ቃለመጠይቅ ተደርጓል።<br><br>ከ አንድ የማኅበረሰብ ተወካይ ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል።<br><br>የተጎጂ ታሪኮች፣ የዕቅድ፣ የሪፖርት እና የወጡ መመሪያዎችን ምልከታና ማገናዘብ ያጠቃልላል። |

| | | |
|---|---|---|
| 7 | በአፋር ክልል፤ በሰመራና ሎግያ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች | ከ14 ሥራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ቃለመጠይቅ ተደርጓል፡፡<br><br>ከ 3 ተጎጂዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡ |
| 8 | በአፋር ክልል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | ከ 2 ባለሙያዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ተድርጓል፡፡ |
| 9 | በኦሮሚያ ክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች | ከ18 የመንግሥት ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ቃለመጠይቅ ተደርጓል፡፡<br><br>5 የተጎጂ ታሪኮች ተካተዋል፡፡ |
| 10 | በኦሮሚያ ክልል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ማቆያ ማእከላት | ከ 4 ባለሙያዎች ጋር ቃለመጠይቅ ተደርጓል፡፡ |

## 4. የክትትሉ ውስንነቶች

ኮሚሽኑ በደኅንነት ሥጋቶች ምክንያት በሰዎች የመነገድ ወንጀል መነሻ፣ መሸጋገርያ እና መዳረሻ የሆኑ ሁሉንም የሀገሪቱ ክፍሎችን በክትትሉ ለመዳሰስ አልቻለም፡፡ በዚህም ሳቢያ በአካባቢያዊና በክስተቶች ሽፋን እንዲሁም በመብቶች ዳሰሳ ረገድ የተሟላ ሪፖርት ለማቅረብ እክል ፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም ክትትል በተደረገባቸውም ቦታዎች ከተቋማት የመረጃ ውስንነት በመኖሩ፣ መረጃ የተሰበሰበበት እና ይህ የክትትል ሪፖርት የተዘጋጀበት ጊዜ የተራራቀ በመሆኑ ሁኔታዎች የተለዋወጡ መሆናቸው፣ በተለይም የቀድሞ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ መንግሥት አዲስ የመንግሥት አወቃቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን አደረጃጀት ለውጥ ያመጣ በመሆኑ በሀገር ውስጥ በሰዎች መነገድ ወንጀል የሚመለከታቸው አካላትም የተቀየሩ መሆናቸው የክትትሉ ዋና ዋና ውስንነቶች ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

# 2. አግባብነት ያላቸው የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች

## 2.1. ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች

ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ከማጽደቅ ጀምሮ በሀገር ደረጃ በሰው መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፎችን አውጥታለች፡፡ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን በተመለከተ፣ ወንጀሉን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ በርካታ ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሕግ እና የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፎች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ዋነኞቹ[5] በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሏዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት፣ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን ለማስወገድ የወጣ የተባበሩት መንግሥታት መግለጫ፣ የአፍሪካ የሰዎች እና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር፣ የአፍሪካ የሰዎች እና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል (የማፑቶ ፕሮቶኮል)፣ በድንበር ተሻጋሪና የተደራጁ ወንጀሎችን ለመቆጣጠር የወጣው የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ ስምምነት[6] እና በሰው በተለይም በሴቶች እና ሕፃናት የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ወንጀል ፈጻሚዎችን ለመቅጣት የወጣ የስምምነቱ ፕሮቶኮል[7] (የፓሌርሞ ስምምነት)፣ በሰው መነገድና የወሲብ ብዝበዛን ለመቆጣጠር የወጣ ስምምነት[8]፣ በዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት በሰዎች የመነገድ ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ ስምምነቶችን ለመደገፍ የግዳጅ ሥራን ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት[9]፣ አስከፊ የሆነ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለመከላከል የተደረገ ስምምነት[10] እና ዝቅተኛ የሥራ ዕድሜን ለመወሰን የወጡ ስምምነቶች[11] ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ስምምነቶች በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 9(4) መሠረት የሀገሪቱ የሕግ አካል ናቸው፡፡ በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ 3 ውስጥ የተረጋገጡ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ከእነዚህ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም እንዳለባቸው ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 13 (2) ይደነግጋል፡፡

በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን ለማስወገድ የወጣው መግለጫ[12] በአንቀጽ 2 በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት በሴቶች መነገድን እንደሚያጠቃልል ያስቀምጣል፡፡ መንግሥትም ሴቶች በታሪክ በነበረ ባልተመጣጠነ የጾታ ግንኙነት እንዲሁም የበታች እንዲሆኑ በሚያስገድዱ ማኅበራዊ ግንኙነቶች ምክንያት ለጥቃት ተጋላጭነታቸውን ታሳቢ ያደረገ የመከላከል እና የመቆጣጠር ሥልቶችን የመቅረጽ ኃላፊነት አለበት፡፡ በተለይም በጥገኝነት፣ በገጠር፣ በድህነት እንዲሁም በጦርነት ወይም በግጭት ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች በሰው ለመነገድ ድርጊት በይበልጥ ተጋላጭ

---

5 The ILO's Forced Labour Convention, 1930 (No. 29), the Abolition of Forced Labour Convention, 1957 (No. 105) ፣ International Labour Organization Guidelines for Legislation and Law Enforcement on human trafficking and forced labor (2005) pp.9.
6 UN Convention Against Transnational Organized Crime, United Nations (2000).
7 Protocol to Prevent, Suppress and Punish Trafficking in Persons Especially Women and Children, supplementing the United Nations Convention against Transnational Organized Crime (Palermo Protocol): Resolution 55/25 (November 15/2000).
8 Convention for the Suppression of the Traffic in Persons and of the Exploitation of the Prostitution of Others.
9 The ILO's Forced Labour Convention, 1930 (No. 29)
10 Worst Forms of Child Labour Convention, 1999 (No. 182) , Abolition of Forced Labour Convention, 1957 (No. 105)
11 Minimum Age Convention, 1973
12 Declaration on the Elimination of Violence Against Women.

በመሆናቸው በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ማናቸውንም አድሏዊ ልዩነት ለማስወገድ የወጣው ስምምነት አንቀጽ 6 ሀገራት ሴቶችን በሕገወጥ መንገድ ማዘዋወር፣ በሴቶች መነገድና ለዝሙት ተግባር ማሰማራትን አስመልክቶ እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለባቸው ይደነግጋል። በተጨማሪም የማፑቶ ፕሮቶኮል ሀገራት ድርጊቱን ለመከላከል፣ ወንጀለኞችን ለመቅጣት፣ በሰው የመነገድ ድርጊት ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችን በይበልጥ ጥበቃ ለማድረግ ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል። በመንግሥት እነዚህ እርምጃዎች ሲወሰዱ፣ ስትራቴጂዎች ሲነደፉ፣ ዕቅዶች ሲወጡና ሲተገበሩ እንዲሁም ያስገኙት ውጤት ሲለካ ከሰብአዊ መብቶች መርሖች እና መንግሥታት ሰብአዊ መብቶች ለማክበር፣ ለማስጠበቅ እና ለማሟላት ከተጣለባቸው ግዴታዎች ጋር ሊጣጣም ይገባል።

በተጓዳኝ ሕፃናት ጤንነታቸውን፣ አካላቸውን እና አእምሮአቸውን እንዲሁም ማኅበራዊ እድገታቸውን በተመለከተ ልዩ ጥበቃ የሚሹ በመሆናቸው ክብራቸውን፣ ደኅንነታቸውን እና ነጻነታቸውን መሠረት ያደረገ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል። በዚህም መሠረት ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ስምምነት፣ አማራጭ ፕሮቶኮሎች እና የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ቻርተር የሕፃናቱን ቤተሰብ ወይም አሳዳጊን ጨምሮ በማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ ሕፃናትን መውሰድና መሸጥ፣ መነገድ ወይም ለማንኛውም ዐይነት የልመና ተግባር መጠቀም የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መሆኑን አስቀምጧል። ሀገራትም ድርጊቱን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት በሚወስዷቸው እርምጃዎች የሕፃናትን ልዩ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት እና ልዩ ፍላጎታቸውን ከግምት ማስገባት እንዳለባቸው ይደነግጋሉ።[13]

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ከዓለም አቀፍ የሕግ ማዕቀፎች ውስጥ በሰው በተለይም በሴቶች እና ሕፃናት የመነገድን ድርጊትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ወንጀል ፈጻሚዎችን ለማስቀጣት የወጣው ፕሮቶኮል (ፓሌርሞ ፕሮቶኮል) በሰዎች የመነገድ ተግባርን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ይደነግጋል። በተመሳሳይም ዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት ከላይ ከተጠቀሱት ስምምነቶች ጋር የሚጣጣሙ የግዳጅ ሥራ ማስቀረትን፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ መከላከልን እንዲሁም ዝቅተኛ የሥራ ዕድሜን የሚወስኑ ስምምነቶችን አውጥቷል።14 እነዚህ ስምምነቶች በተለይም የፓሌርሞ ፕሮቶኮል አንቀጽ 2 በሀገራት ውስጥ በሰዎች የመነገድ ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚተገበሩ እርምጃዎች ለሴቶች እና ለሕፃናት ልዩ ትኩረት ሊሰጡ እንደሚገባ ያስቀምጣሉ።

በሰው የመነገድ ድርጊት ተጋላጭና ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት የሌሎች ተደራራቢ የመብት ጥሰቶችም ተጎጂዎች ናቸው። በዋነኝነትም ሴቶችና ሕፃናት በሰዎች የመነገድ ወንጀል ሰለባ ሲሆኑ የእኩልነት፣ አድሏዊ ልዩነት ያለማድረግን፣ የሕግ የበላይነት መለኪያን በማድረግ የሴቶች እና ሕፃናትን በሕይወት የመኖር መብት፣ የነጻነትና የአካል ደኅንነት፣ የአካልና የአእምሮ ጤንነት መብት እንዲሁም ከማሰቃየት ተግባር ወይም ጭካኔ ከተሞላበትና ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ እና ቅጣት የመጠበቅ መብቶቻቸው ይጣሳሉ። በተለይም ሕፃናት የወላጆች

---

13 የሕፃናት መብቶች ስምምነት አንቀጽ 36 እና የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደኅንነት ቻርተር አንቀጽ29 ያመላክታሉ፡፡ የሕፃናት መብቶች ስምምነት አማራጭ ፕሮቶኮል በአንቀጽ 1 እና 2።

14 The ILO's Forced Labour Convention, 1930 (No. 29), the Abolition of Forced Labour Convention, 1957 (No. 105); Worst Forms of Child Labour Convention No. 182; Domestic Workers Convention No. 189; the Private Employment Agencies Convention No. 181; International Labour Organization Guidelines for Legislation and Law Enforcement on human trafficking and forced labor (2005) pp.9

እንክብካቤና ጥበቃ የማግኘት መብታቸው (የሕፃናቱን ጥቅም የሚያስጠብቅ ሆኖ ሲገኝ)፣ ከጥቃት የመጠበቅ፣ ከአካላዊ ቅጣት የመጠበቅ፣ ትምህርት የማግኘት፣ ጤናን እና እድገትን ሊጎዳ እንዲሁም ጉልበትን ሊበዘብዝ ከሚችል ሥራና የኑሮ ሁኔታ የመጠበቅ መብቶቻቸውን ያጣሉ።

## 2.2. በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ተፈጻሚነት ያላቸው ዓለም አቀፍ መመዘኛዎች

በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚተገበሩ እርምጃዎች ሰብአዊ መብቶችን መሠረት ባደረገ መልኩ መተግበር አለባቸው። ይህንኑ አሠራር እና አተገባበር የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ የአተገባበር መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል። የፓሌርሞ ፕሮቶኮል አንቀጽ 2 ሀገራት በሰዎች መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚተገበሩ እርምጃዎች ሴቶች እና ሕፃናት ላይ ትኩረት ያደረጉ፣ የተጎጂዎች ጥበቃ እና የድጋፍ ሥራዎች ሰብአዊ መብቶችን ማእከል ባደረገ መልኩ፣ የመከላከል እና የመቆጣጠር ሥራዎች ደግሞ በተቋማት መካከል ያለን ትብብር እና አጋርነት በሚያጠናክር መንገድ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል። ምንም እንኳን አንቀጽ 5 የፕሮቶኮሉን የአፈጻጸም ወሰን ድንበር ተሻጋሪ የሆኑትን ወንጀሎች እና በተደራጁ ቡድኖች የሚፈጸሙትን በሰው የመነገድ ድርጊቶች ብቻ የሚመለከት ቢመስልም በፕሮቶኮሉ አንቀጽ 3 በሰዎች ለመነገድ የተሰጠው ትርጉም በሀገር ውስጥ የሚካሄደውንም ሆነ ድንበር ተሻጋሪ የሆነውን ድርጊት የሚሸፍን ነው። የተደራጁ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ለመከላከል በጸደቀው የተባበሩት መንግሥታት ስምምነት አንቀጽ 34 መሠረት ሀገራት በሰዎች የመነገድ ድርጊትን በብሔራዊ ሕጎቻቸው ወንጀል በሚያደርጉበት ወቅት በሀገር ውስጥ ሚከናወነውንም ሆነ ድንበር ተሻጋሪውን እንዲሁም በተደራጁ ቡድኖችም ሆነ በግለሰብ የሚፈጸመውን ሁሉ እንዲያጠቃልል ያስቀምጣል።[15]

መንግሥታት በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን ለመከላከል ሕጋዊ፣ ፖለቲካዊ፣አስተዳደራዊ እና ማኅበራዊ ፀባይ ያላቸውን ሰፊ ሥልቶችን መንደፍ አለባቸው። መንግሥታት በሰው የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አራት ዐበይት እርምጃዎችን መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። ይህም በሰው የመነገድ ድርጊትን በተመለከተ ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ፦

- ድርጊቱን በብሔራዊ ሕግጋት ወንጀል ማድረግን ጨምሮ ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመውሰድ፤
- ለተጎጂዎች ድጋፍ እና የጥበቃ እርምጃዎችን የማመቻቸት፤
- የወንጀል ምርመራ በማድረግ የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ማረጋገጥ እንዲሁም
- እነዚህን ሥራዎች ለመሥራት የትብብር ማዕቀፍ የመዘርጋት ግዴታ እንዳለባቸው ያስቀምጣል።

---

[15] Protocol to Prevent, Suppress and Punish Trafficking in Persons Especially Women and Children, supplementing the United Nations Convention against Transnational Organized Crime (Palermo Protocol): Resolution 55/25 (November 15/2000) and Legislative Guideline and United Nations Convention against Transnational Organized Crime.

### 2.2.1. በሰዎች የመነገድ ድርጊትን በብሔራዊ ሕግጋት ወንጀል ማድረግን ጨምሮ ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመውሰድ ግዴታ

መንግሥት በሰዎች የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀር፣ የድርጊቶቹን መንስዔዎች፣ ባሕርያት፣ ክብደት እና ውጤቶችን የተመለከቱ ጥናቶችን በማከናወንና በማበረታታት ለሕዝብ ይፋ የማድረግ ተቀዳሚ ኃላፊነት አለበት፡፡ የፓሌርሞ ፕሮቶኮል ሀገራት በሰው ለመነገድ ድርጊት ተግባራዊ የሚደረጉ መንገዶችን፣ ዘዴዎችን እና የሚደረግበትን ዓላማ ጭምር ወንጀል ማድረግን ያስገድዳል፡፡[16] ሀገራት ድርጊቱን መፈጸምን፣ በተባባሪነት መሳተፍን፣ ወንጀሉ እንዲፈጸም ሌሎች ሰዎችን በማስተባበር ወይም በማደራጀት እና በማዘዝ መሳተፍን ወንጀል ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህም መሠረት በመከላከል እርምጃው በዋናነት፡-

- በሰዎች የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል፣ ወንጀሉን የፈጸሙትን በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ እና ለተጎጂዎች ካሳን ጨምሮ አግባብ ያለው ጥበቃና ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ሕጎችን፣ የብሔራዊ ድርጊት መርኀ-ግብሮችን መንደፍ፤
- በሴቶች እና ሕፃናት የመነገድ ድርጊቶች አባባሽ፣ መጋቢ ወይም ሳቢ የሆኑ ምክንያቶችን እና መንስዔዎችን መለየት፤
- ለመንግሥት አስፈጻሚ አካላት፣ ለሕዝቡ በተለይም ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት ትምህርት እና ሥልጠናዎችን መስጠት፣ እንዲሁም የሥራ ዕድሎች መፍጠር፤
- ለመከላከል ተግባራዊ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ለመደገፍ በቂ ሀብት በመንግሥት በጀት ውስጥ ማካተት እንዲሁም ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰቡ ማሰባሰብ እንዲሁም፤
- የመከላከል እርምጃዎች የታለመላቸውን ዓላማ እያሳኩ መሆኑን ለማረጋገጥ መደበኛና ሥልታዊ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ ይገባል፡፡

---

[16] የፕሮቶኮሉ አንቀጽ 3 እና 5 በፕሮቶኮሉ መሠረት ማንም ሰው ለብዝበዛ ዓላማ ሰውን በማስፈራራት፣ በመጥለፍ፣ በማጭበርበር፣ በማታለል፣ የተጋላጭነትን ሁኔታን ወይም ሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀም፣ በእዳ መያዣ ለማድረግ በአንድ ሰው ላይ ቁጥጥር ያለውን ሰው ፈቃድ ለማግኘት ገንዘብ በመስጠት ወይም በመቀበል፣ መመልምልን፣ ማጓጓዝን፣ ማስተላለፍን፣ መያዝን እና መቀበልን ወንጀል መደረግ እንዳለበት ያስቀምጣል። በፕሮቶኮሉ የተገለጹት የብዝበዛ ዐይነቶች የተሟሉ ባይሆኑም የግዳጅ ሥራ ወይም አገልግሎት፣ ባርነት ወይም ባርነት መሰል ተግባር፣ አገልጋይነት፣ አካልን ማውጣት የሚያጠቃልል እንደሆነ ያስቀምጣል።

### 2.2.2. ለተጎጂዎች ድጋፍ እና የጥበቃ እርምጃዎችን የማመቻቸት ግዴታ

መንግሥት ለተጎጂዎች ጥበቃ እና ድጋፍ የማድረግ ግዴታውን ሲወጣ ሰብአዊ መብቶችን ባከበረ መልኩ ሊሆን ይገባል። በዚህም መሠረት መንግሥት ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር ትብብር በመፍጠር፡-

- የተጎጂዎች ልየታ ማከናወን፣ የሚሰጡ አገልግሎቶች የተጎጂዎችን ሚስጥርና ደኅንነት፣ በአዘዋዋሪዎች ሊደርስባቸው የሚችልን ዳግም ጥቃትን ታሳቢ ያደረገ ውጤታማ መዋቅር መፍጠር፤
- ተጎጂዎች ከደረሰባቸው የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ለማቋቋም፣ ለሕፃናት እንክብካቤና የመተዳደርያ ድጋፍ፣ መጠለያ፣ ምግብ፣ የሕክምና አገልግሎት፣ የምክር፣ ሥነ ልቦናዊ ተሐድሶ እንዲያገኙ ማስቻል፤
- ሊደርስባቸው የሚችሉትን የመገለል ሁኔታ ለመቀንስ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ እርምጃዎችን መውሰድ፤
- የተጎጂዎችን ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ በፍትሕ ሥርዓት ሐሳባቸው እንዲሰማ እና ከግምት እንዲገባ፣ የጉዳት ካሳ በሚጠይቁበት ሁኔታ እንዲታገዙ፣ የሚሰጣቸው ድጋፍ እና ጥበቃ ፈቃዳቸውን መሠረት ያደረገና ተጎጂዎች ለፍትሕ አካሉ የሚያደርጉት ትብብር እንደ ቅድመ ሁኔታ የተቀመጠ ሊሆን እንዳማይገባ ተቀምጧል።

### 2.2.3. የወንጀል ምርመራ በማድረግ የአጥፊዎችን ተጠያቂነት የማረጋገጥ ግዴታ

በብሔራዊ የወንጀል ሕግጋት በሰዎች የመነገድን ድርጊት ወንጀል ማድረግ ያለፈጻሚ አካላት ጉልህ ሚና ውጤት አይኖረውም። በመሆኑም በሕግ የተቀመጡ መብቶች እና ግዴታዎች እንዲፈጸሙ የተቆጣጣሪ አካላት፣ የፖሊስ፣ የፍርድ ቤቶች፣ የሰብአዊ መብቶች ተቋማት ሚና ወሳኝ ሲሆን ወንጀሎች መፈጸማቸውን ከመለየት እና መርምሮ ከማስቀጣት አንጻር ደግሞ የፖሊስ እና የዐቃቤ ሕግ ሚና ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛል። ይህን ለማድረግ የሕግ እና ተቋማዊ አሠራር መኖር እንዲሁም የወንጀል አፈጻጸሙን ለመለየት እና ለመመርመር የሚያስችል ስልጠና በመስጠት ተገቢውን ዕውቀት ለፈጻሚ አካላት እንዲያስጨብጡ ይጠበቃል።

### 2.2.4. የትብብር ማዕቀፍ የመዘርጋት ግዴታ

መንግሥት በተለይም በሴቶች እና ሕፃናት መብቶች ላይ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ትብብርን በመፍጠር የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራዎችን ማቀናጀት ይኖርበታል። የትብብር ሥራዎች መንግሥት ውጤታማ የምርመራ፣ የክስ፣ የተጎጂዎች ድጋፍ እና ጥበቃ፣ የመከላከል ሥራን ለማረጋገጥ ፣ የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን የሚያሳትፍ እና እንደሁኔታው ተለዋዋጭ መሆን የሚችል፣ የተደራጀ እና ሁሉን አቀፍ ትብብር መኖር አለበት።

## 2.3. በሰዎች የመነገድ ድርጊትን የተመለከቱ የኢትዮጵያ የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.) ሕገ መንግሥት አንቀጽ 18(2) መሠረት ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም። በዚህም ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ መሆኑን ይደነግጋል። በ1997 በወጣው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ሕግ በሰው የግል ነጻነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሚል ክፍል በአንቀጽ 596 'ሰውን አገልጋይ ማድረግ' እና 597 'በሴቶች እና በልጆች መነገድ' በሚል በሰዎች የመነገድን ድርጊትን በወንጀልነት ደንግጓል። ሆኖም በዚህ ጉዳይ የወንጀል ሕጉ ከዓለም አቀፍ ሰነዶች ጋር የተጣጣመና የተሟላ ሕግ ሆኖ ባለመገኘቱ በሰው መነገድ እና ሰውን በሕገወጥ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ወጥቷል። አዋጁ የወንጀሉ ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና መልሶ ማቋቋም ሊደረግላቸው ይገባል በሚል አዋጅ ቁጥር 909/2007ን በመሻር ተሻሽሎ የወጣ ነው። ዓላማውም በሰው የመነገድ ድርጊትን በተለይም በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ወንጀል ፈጻሚዎችን ለመቅጣት፣ ለተጎጂዎች ጥበቃ ለማድረግ እና መልሶ ለማቋቋም የታሰበ ነው። ነገር ግን አዋጅ 1178/2012 በአንቀጽ 3 በሰው ለመነገድ ወንጀል የሰጠው ትርጉም በፓሌርሞ ፕሮቶኮል ከተቀመጠው ትርጓሜ ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ፤ በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 11/2013 በሰው ለመነገድ ወንጀል የተሟላ ትርጉም መስጠት ተችሏል። በዚህም ማንኛውም ሰው፦

- ሌላውን ሰው በባርነት ወይም በባርነት መሰል ተግባር፣ በአገልጋይነት ወይም በዕዳ መያዣነት ለመያዝ፣ አካሉን በማውጣት ወይም በዝሙት አዳሪነት ወይም መሰል የወሲብ ተግባር ብዝበዛ ለመፈጸም፣ በግዳጅ ሥራ ወይም አገልግሎት፣ በልመና፣ በወንጀል ተግባር፣ በግዳጅ ጋብቻ፣ ወይም በማሕጸን ኪራይ ለማሰማራት ወይም ሕፃናትን በጉልበት ሥራ ለመበዝበዝ ወይም እነዚህን መሰል የብዝበዛ ተግባራት ለመፈጸም፤ (የመበዝበዝ ዓላማ)
- በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ግዛት ውጪ መዳረሻ ቦታ ለማድረስ፤ (በሀገር ውስጥም ሆነ ድንበር ዘለል)
- በዛቻ፣ በኃይል፣ በማገት፣ በመጥለፍ፣ ወይም ሌላ የማስገደጃ ዘዴ በመጠቀም፣ በማታለል፣ የተስፋ ቃል በመስጠት፣ ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀም፣ የሰውን ተጋላጭነት በመጠቀም ወይም ስለሌላው ኃላፊነት ያለበትን ሰው ፈቃድ ለማግኘት መደለያ ወይም ጥቅም በመስጠት ወይም በመቀበል፤ (የተለያዩ መንገዶች በመጠቀም)
- ሌላውን ሰው የመለመለ፣ ያጓጓዘ፣ ወደ ሌላ ያስተላለፈ፣ ያስጠለለ፣ የደበቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ (የተከለከሉ ተግባራት)

በሰው መነገድ  የወንጀል ድርጊትን እንደፈጸመ የሚቆጠር ሲሆን ይኸውም ከሰባት ዓመት እስከ አስራ ሁለት ዓመት በሚደርስ  ጽኑ እስራትና ከአርባ ሺህ እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል።

የአዋጁ አንቀጽ 3(3) ሕፃናት ልዩ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው በመገንዘብ ከላይ የተጠቀሱት መንገዶች ጥቅም ላይ ባይውሉም፤ ማለትም ዛቻ፣ ኃይል፣ ማገት፣ መጥለፍ፣ ወይም ሌላ የማስገደጃ ዘዴ መጠቀም ወዘተ፤ ሕፃናትን ለብዝበዛ ዓላማ መመልመል፣ ማጓጓዝ፣ ወደ ሌላ

ሰው ማስተላፍ፣ ማስጠለል፣ መደበቅ ወይም መቀበል በሰው የመነገድ ድርጊት ያደርጋል፡፡ ይህም ማለት ተጠቂ ሕፃን ከሆነ/ች የተሟላ ፈቃድ እንዳልነበረ ማሳየት አያስፈልግም፡፡

በተጨማሪ አዋጅ ቁጥር 1178/2012ን ለማስፈጸም የሚያግዙ ሁለት መመሪያዎች፦ የብሔራዊ የተጎጂዎች የቅብብሎሽ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 562/13 እንዲሁም የሥራ ቡድኖችን ለማደራጀትና አባላትን፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 563/13 ተዘጋጅተዋል፡፡ ውጤታማ፣ ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ሰብአዊ ክብር ላይ የተመሠረተ የፍልሰት አስተዳደር ሥርዓት ለመዘርጋት ብሔራዊ የፍልሰት ረቂቅ ፓሊሲ ተዘጋጅቶ ለሚኒስተሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲም ወንጀል ለመከላከል፣ ተፈጽመው ሲገኙ ለመመርመርና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ፣ ዓለም አቀፍ ትብብር እና ድጋፍ ማድረግ፣ ለተጎጅዎች ጥበቃና ድጋፍ የማድረግ ተግባራት በዓለም አቀፍ እና በሕገ መንግሥቱ በተቀመጡ የሰብአዊ መብቶች መርሖች መሠረት መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡[17] በተጨማሪም በፖሊሲው 1.4(በ) በወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ በማንኛውም ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት የሴቶች እና ሕፃናት ተጎጅዎችን ፍላጎት እና የተለዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ትኩረት ማግኘታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ መሆን እንዳለበት ገልጿል፡፡ ይህም በሰዎች የመነገድ ድርጊት ተጎጂ ለሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት ምላሽ በመስጠት ረገድ እንደ ጥሩ መነሻ የሚጠቀስ ነው፡፡

[17] በሰው መነገድ እና ሰውን በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀሎች ላይ ለፍትሕ አካላት የተዘጋጀ የሥልጠና ማንዋል፡፡ (ፍትሕ ሚኒስቴር ከ GIZ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ) 2014 ዓ.ም.

# ክፍል ሦስት

## 3. ዋና ዋና ግኝቶች

### 3.1. በሰው መነገድ ወንጀል ተጎጂዎች እና የደረሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች

ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ሴቶችን ኢላማ አድርገው የሚሠሩ በሰው የመነገድ አዘዋዋሪዎች የሴቶቹን ሥራ አጥነት፣ በዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ የሚገኙ እና በቂ መረጃ የማያገኙ መሆናቸውን በመገንዘብ እንደሚመለምሏቸው፣ እንዲሁም ስለመዳረሻ ቦታዎች የተዛባ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ (በማታለል) ወደ ሌሎች አዘዋዋሪዎች ወይም አሠሪዎች እንደሚያስተላልፏቸው ተረድቷል:: ተጎጂ ሴቶች በተሳሳተ መረጃ ከፈለሱ በኋላ ያለሙትን ሕይወት ከማግኘት ይልቅ በአብዛኛው በወሲብ ንግድ፣ በጉልበት ሥራ፣ በቤት ሠራተኝነት፣ በሽመና ሥራ፣ በጫት ለቀማ በመሳሰሉት እንደሚሠማሩ ከተጎጂዎች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ ያሳያል:: በተሠማሩበት ሥራዎችም ያለ በቂ ዕረፍት እና ክፍያ እንደሚሠሩ፣ ድብደባና ስድብ እንዲሁም ሌሎች አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጥቃት እንደሚደርስባቸው ኮሚሽኑ በክትትል ያገኘው መረጃ ያመላክታል:: ተጎጂዎች ውጤታማ የፍትሕ አገልግሎት ባለማግኘታቸውም በፍትሕ ሂደት ለዳግም በሰው የመነገድ ድርጊትና ጥቃት ይጋለጣሉ::

ሕፃናትን ኢላማ አድርገው የሚሠሩ አዘዋዋሪዎች ሕፃናት ከቤተሰብ ወይም አሳዳጊ ቁጥጥር ውጪ ያሉ መሆናቸውን፣ የአካል እና የአእምሮ እድገታቸው ያልዳበረና ተጋላጭ በመሆናቸው፣ የራሳቸውን እና የወላጆቻቸውን የኑሮና ኢኮኖሚ ችግሮችን መሠረት በማድረግ፣ በግጭትና ጦርነት ተፈናቃይ መሆናቸውና ከቅርብ ቤተሰቦቻቸው የተለዩ መሆናቸውን በማየት፣ ከትምህርትና መረጃ የራቁ የሕፃናት ጉልበት ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው መሆኑን ከግምት በማስገባት የወላጆቻቸውን ሕይወት ለመቀየር የሚያስችላቸው የሥራና የትምህርት ዕድሎች እንደሚያገኙ ቃል በመግባት በተለያዩ ሥራዎች ያሠማሯቸዋል:: በተጨማሪም ሕፃናት በወላጆቻቸው ፍቃድ ወይም በመዳረሻ ከተሞች በሚኖሩ ዘመዶቻቸው እናስተምራችኋለን በሚል ተወስደው ያለሙትን ትምህርት ሳያገኙ ያለ በቂ ክፍያ እና ዕረፍት በቤት ውስጥ ሥራ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም በሚያስገኙ የጎዳና ላይ ንግዶች እንዲሠማሩ ይደረጋሉ:: በእነዚህ ሥራዎችም ለወሲብ ጥቃት፣ ለጉልበት ብዝበዛ፣ ለአካላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ጥቃቶች እንደሚጋለጡ ታውቋል:: ለአብነትም በቀድሞው ደ/ብ/ብ/ክ መንግሥት በአሁኑ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ በወላይታ ዞን በተደረገው ክትትል አዘዋዋሪዎች ሕፃናትን ኢላማ አድርገው እንደሚሠሩ እና ወላጆችም በሂደቱ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ዕድሎች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል:: ካሉበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማጓጓዝ የሕዝብ መጓጓዣ ትራንስፖርቶች፣ የግለሰብ መጓጓዣዎችን በመከራየት ወይም አንዳንድ ጊዜ ኬላዎች ላይ ከሚገኙ ተቆጣጣሪዎች ለማምለጥ በሚል እስከተወሰነ ቦታ በእግር መንገድ እንደሚያጓጉዟቸው ከተጎጂዎች፣ ከመጠለያ ማእከላት እና ከወላይታ ዞን ሴቶች፣ ሕፃናትና አረጋውያን መምሪያ ያገኘናቸው መረጃዎች ያመላክታሉ:: በምልመላና በማጓጓዝ ሂደቱ የአሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ፍቃድ የሌላቸው ግለሰቦች (ደላሎች) እንደሚሳተፉ ለማወቅ ተችሏል:: ኮሚሽኑ በአፋር ክልል ባከናወነው ክትትል ከወላይታ ዞን ሕፃናት በአዘዋዋሪዎች ተታለው ወደ አፋር ክልል እንደሚወሰዱ እና ለጉልበት ብዝበዛ በሚያጋልጡ ሥራዎች እንደሚሠማሩ ለመረዳት

ተችሏል፡፡ በተለይም ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑት ሕፃናት በቂ ዕረፍት፣ተመጣጣኝ እና በቂ ክፍያ በማያገኙበት፣ለሌሎች ግለሰቦች ጥቅም በሚያስገኙ የጫማ ማሳመር ወይም ሊስትሮ ሥራ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ በክትትል የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በአዲስ አበባ በተደረገው ክትትል ለሀገር ውስጥ በሰው መነገድ አዘዋዋሪዎች ሴቶች እና ሕፃናትን የተሻለ የሥራ እና የትምህርት ዕድል እንደሚያገኙ ቃል ገብተው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለብዝበዛ ዓላማ ይመለምሏቸዋል፡፡ ኢሰመኮ ከፌዴራል ፖሊስ ያገኘው ማስረጃም ተጎጂዎችን ቁጥጥር በማይደረግባቸው በ'ኢ-መደበኛ' ሥራዎች በዋናነት በቤት ውስጥ ሥራ፣ በሽመና እና በሚዛን ሥራ እንደሚያሠማሩዋቸው እና አካላዊና ወሲባዊ ብዝበዛዎች እንደሚደርስባቸው ጥቆማዎች ደርሰውት እንደሚያቁ ለመረዳት ችሏል፡፡ በባሕር ዳር በተደረገው ክትትል በባሕር ዳር ከተማ በዝውውር ሰንሰለት ሂደት ሕፃናትን ተቀባዮች እንዳሉ፣ በዋናነትም በሕዝብ ትራንስፖርት መናኀሪያ ቦታዎች ያሉ 'ደላሎች' ለአሠሪ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች እንደሚያቀብሏቸው ታይቷል፡፡ ተጎጂዎች በባሕር ዳር ከተማ በቤት ሠራተኝነት ወይም በአብዛኛው 18 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ሰፋፊ የእርሻ ሥራ ወደሉባቸው አካባቢዎች ለምሳሌ ቋራ እና መተማ እንደሚላኩ እና በእነዚህ የሥራ መስኮች ለረዥም ሰዓት ሥራ እንደሚሠሩ፣ ደመወዝ እንደሚከለከሉ፣ ለአካላዊ ቅጣት እና ለሥነ-ልቦና ጉዳት እንደሚዳረጉ ከተጎጂ ማእከላት እና ከፍትሕ አካለት የተገኙ መረጃዎች አመላካች ናቸው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም በአዳማ ከተማ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆኑ ሕፃናት ከገጠር አካባቢዎች የተሻለ የሥራ እና የትምህርት ዕድል ለማግኘት በሚል ተታለው ወደ ከተማ በመምጣት ለወሲብና ጉልበት ብዝበዛ በሚዳርጓቸው የተለያዩ ሥራዎች ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ፡፡ ከአዳማ ከተማ ፖሊስ የሴቶች እና ሕፃናት ጉዳይ ኃላፊ የተገኘው መረጃ በተለይም በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን እና ጅማ ከተማ እንዲሁም በቀድሞ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በአሁኑ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ ወላይታ ዞን የሚንቀሳቀሱ አዘዋዋሪዎች አዳማ ከተማን መዳረሻና መሸጋገርያ እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል፡፡

ለምሳሌ በባሕር ዳር በሚገኙ ሁለት የተጎጂ ማእከላት ቃለ መጠይቅ ካደረግንላቸው ሕፃናት መካከል አንድ የ11 ዓመት ሕፃን አስተምራታለሁ በሚል ከምትኖርበት አካባቢ ወደ ባሕር ዳር ከተማ ያመጧት መሆኑንና የቤት ውስጥ ሥራ እንድትሠራ እና ቤተሰብ በሚያከናውነውን የባጃጅ ባትሪ አሲድ የመሙላት ንግድ ሥራ የማገዝ ኃላፊነት ያለባት በመሆኑ ለከፍተኛ አደጋ የሚያጋልጥ ሥራ ላይ እንዳሠማሯት፣ እንቅልፍ በሚያስቸግራት ወቅትም አይኗ ላይ አሚር እንደሚጨመርባትና ቤት ውስጥ ካሉ ሕፃናት ጋር ስትጫወትም ድብደባ እንደሚደርስባት ለኮሚሽኑ አስረድታለች፡፡ ጉዳዩ ፖሊስ ጋር ቢደርስም ክስ የተመሠረተው ቀላል የአካል ጉዳት በማድረስ ወንጀል እንጂ በሰው በመነገድ ተግባር አለመሆኑን ኮሚሽኑ ተረድቷል፡፡ በተመሳሳይ ለተሻለ ሥራ በሚል ቋራ ወደተባለ ቦታ የተዘዋወረች የ16 ዓመት ልጅ አዘዋዋሪው የአስገድዶ መድፈር ሙከራ እንዳደረሰባት፤ በምርመራ ሂደት ሴቶችን ለሥራ በመላክ ሂደት ውስጥ በሰዎች መነገድ የሚያሚላ ድርጊት መፈጸሙን ለመመርምር እና ለማጣራት መነሻ ሊሆን የሚችል አመላካች ወይም ፍንጭ ሰጪ ማስረጃ ቢገኝም ወንጀሉን የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ ግን ምርመራ እና ማጣራት አለመካሄዱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡[18]

---

[18] በክትትሉ ግለሰቡ ሕጋዊ ሥራ አሠሪን ለማገናኘት ፍቃድ እንደሌለው ሆኖም ሕፃናት 'ለሥራ' እንደሚልክ ለመረዳት ተችሏል። ሆኖም የወንጀል ምርመራ ሂደቱ በመጠናቀቁ በሰው የመነገድ ድርጊት ትርጓሜ መሠረት የማዘዋወር ዓላማውን ለይቶ ለመረዳት አልተቻለም።

## 3.2. በሀገር ውስጥ የሚደረግ በሴቶችና በሕፃናት የመነገድ ድርጊት የባለግዴታዎች ምላሽ አሰጣጥን የተመለከቱ ዋና ዋና ግኝቶች

### 3.2.1. በሰዎች የመነገድ ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችሉ የሕግ እና የፖሊሲ ማዕቀፎች

መንግሥት በሰዎች የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችን፣ ፕሮግራሞችን፣ የብሔራዊ ድርጊት መርኃ-ግብሮችን መንደፍና መተግበር ሊወስድ ከሚገባቸው መሠረታዊ እርምጃዎች አንዱ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ብሔራዊ የፍልሰት ፖሊሲ መረቀቅ፣ የፍልስት አስተዳደር የአምስት ዓመት የስትራቴጅክ ዕቅድ (2013 — 2017 ዓ.ም.)፣ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂ እና የተጎጂዎች ፈንድ አስተዳደር ደንብ መዘጋጀት፣ በሰው መነገድን ተከላካይ ብሔራዊ የትብብር ጥምረት መቋቋም እንዲሁም ከዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች መርሖችና ስምምነቶች ጋር ለማጣጣም በሰዎች የመነገድ እና ሰውን በሕገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገርን የሚመለከተው አዋጅ 909/2007 ተሻሽሎ አዋጅ 1178/2012 መውጣት፣ እንዲሁም በሰው የመነገድ ተግባርን ከፓሌርሞ ፕሮቶኮል ጋር የተጣጣመ ትርጉም ለመስጠት በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 11/2013 መውጣት የታዩ መልካም እመርታዎች ናቸው፡፡ በአዋጅ 1178/2012 በሰው የመነገድ፣ ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር እና በሕገ ወጥ መንገድ ሰውን ለሥራ ወደ ውጭ መላክ ወንጀልን መከላከልና መቆጣጥር፣ በብሔራዊ ደረጃ አስተባባሪ ምክር ቤት እና የትብብር ጥምረት መቋቋም፤ በሰው የመነገድ ድርጊትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ፖሊሲ፣ ሕግ እና ስትራቴጂ ለማመንጨት እና ጠቅላላ ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ ለመምራት አስቻይ ሁኔታን እንደሚፈጥር ኢሰመኮ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም በ2014 ዓ.ም. የረቀቀው ብሔራዊ የፍልሰት ፖሊሲ ጭብጦች፣ የትኩረት ነጥቦች፣ ስትራቴጂዎች በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን በተመለከተ ግልጽ የፖሊሲ መመርያዎችን አላስቀመጠም፡፡ አዋጅ ቁጥር 1178/2012ን መሠረት በማድረግ የሥራ ቡድኖችን ለማደራጀትና አባላትን፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው መመርያ ቁጥር 563/13 በጥቅሉ በሰዎች የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የመንግሥት አካላትን ሚና ያስቀመጠ ቢሆንም በሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ድርጊትን በተመለከተ ትኩረት አድርጎ የመንግሥት አካላት ያላቸውን ሚና በግልጽ አያስቀምጥም፡፡ የብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ የ2015 ዓ.ም.ዓመታዊ ሪፖርቱን ሲያቀርብ ያጋጠሙ ችግሮች ብሎ ከለያቸው ውስጥ ከወንጀል መከላከል እና ሕግ ማስከበር አንጻር በሀገር ውስጥ በሰው የመነገድ ድርጊት የተሰጠው አናሳ ትኩረት፣ ከትብብር ጥምረቱ አባል ተቋማት ጋር በተያያዘ ተወካዮቻቸው በየጊዜው መቀያየራቸው፣ መመሪያው በሚያዘው መሠረት ውሳኔ መስጠት የሚችሉ እና ሥራ የሚመሩ ኃላፊዎችን ያለመመደብ፣ ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ተወካዮችን መመደብ፣ በተቋም ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት አለማስተባበር፣ ራሱን እንደቻለ አንድ ሥራ አለመቁጠር፣ መረጃ በአግባቡ ያለመያዝ፣ የተጠያቂነት ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ የሥራ ቡድን መሪ ተቋማት መሪነታቸውን በሚፈለገው ልክ አለመወጣት፣ በመመሪያው መሠረት የቡድኖች ስብሰባዎች አለመካሄዳቸው እና ሀገራዊ ሪፖርቶችን ለማጠናቀር የመረጃ ችግሮች ማጋጠማቸው የሚሉት ይገኙበታል፡፡

አዋጁ በጥቅሉ በሰው የመነገድ ድርጊት ተጎጂዎች ጥበቃ ለማድረግ እና መልሶ ለማቋቋም ባስቀመጣቸው ድንጋጌዎችም ሆነ አዋጁን ተከትሎ በወጣው ከፍልሰት ተመላሽ የመልሶ ማቋቋሚያ መመርያ ቁጥር 969/2015 ትኩረቱን ያደረገው ከውጭ ሀገር ተመላሾች ላይ በመሆኑ በሀገር ውስጥ በሰው የመነገድ ድርጊት ተጎጂ ለሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት የጥበቃ እና መልሶ የማቋቋም ሥራዎችን የተመለከቱ ግልጽ ድንጋጌዎች የሉትም፡፡

የብሔራዊ የትብብር ጥምረት የፍልሰት አስተዳደር ከ2013 - 2017 ዓ.ም. ባወጣው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ በሀገር ውስጥ በሰው የመነገድ ወንጀል በተለይ በሕፃናት ላይ የሚፈጸመው ትኩረት የሚያሻው መሆኑን ዕውቅና ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ይህን ለማሳካት በአምስት ዓመቱ የታቀዱትን እርምጃዎች በሀገር ውስጥ ሰው መነገድን ለመከለላከል እና ለመቆጣጠር የሚተገበሩ አቅጣጫዎችን አላሳዩም፡፡ አዋጅ ቁጥር 1178/2012ን መሠረት በማድረግ የወጣው የተጎጅዎች ብሔራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 562/2013 ተጎጅዎችን ለማዳን፣ ለመመለስ፣ መልሶ ለማቋቋም ተግባራዊ ስለሚደረግ የቅብብሎሽ ሥርዓት እና የተቋማት ኃላፊነት በዝርዝር ያስቀመጠ ቢሆንም መመርያው በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት የመነገድ ድርጊት ተጎጂዎችን በተመለከተ ቅብብሎሹ በምን ሥርዓት እንደሚመራ፣ የግዴታ ፈጻሚ አካላት ኃላፊነት ምን ምን እንደሆነ በግልጽ አላስቀመጠም፡፡

በኢትዮጵያ በሰው የመነገድ ድርጊቶች መንስዔ ከሆኑት መካከል በዋነኝነት የሚጠቀሱት ሥራ አጥነት፣ ድህነት፣ የቤተሰብ እና የአቻ ግፊት እና የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች እንደሆኑ የመንግሥት ሪፖርቶች እና የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህን ለመከላከል መወሰድ ካለባቸው እርምጃዎች አንዱ የሀገር ውስጥ የሥራ ስምሪት ሥርዓትን በሕግ መወሰን ነው፡፡ በዚህ ረገድ የአሠሪ እና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ሴቶች እና ሕፃናት በሰፊው የሚሠማሩባቸው የግል አገልግሎት ቅጥርን ከተፈጻሚነት ወሰኑ ውጪ አድርጎታል፡፡ ይህንን የሥራ ዘርፍ የሚመራ የሕግ ሥርዓት እና ዘርፉን በቀጥታ ለመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው ተቋም አለመኖሩን በክትትሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 3.2.2. የጥናትና ምርምር ሥራዎች

መንግሥት በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ተጎጂዎችን ለማቋቋም፣ ወንጀል ፈጻሚዎች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ለማስቻል እና ሁሉን አቀፍ ሳይንሳዊ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል የጥናትና ምርምር ሥራዎች ማካሄድ ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 የጥናትና ምርምር ተግባሩን ለመምራት ኃላፊነት የተጣለበት የትምህርት ሚኒስቴር ክትትል እስከተደረገበት ወቅት ድረስ በጉዳዩ ላይ የተከናወነ ጥናትና ምርምር እንደሌለ አሳውቋል፡፡ በወላይታ ዞን በሰዎች ለመነገድ ድርጊት ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ለመለየት የተካሄደውና በኃላፊዎች ለኮሚሽኑ ከደረሰው ጥናት ውጪ በክልሎች ይህን ሥራ እንዲሠሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው መንግሥታዊ የፍትሕ ጥናትና ምርምር ተቋማት ዘንድ የንድፈ ሐሳብ ዝግጅት ጅምሮች መኖራቸው የተገለጸ ቢሆንም፣የተጠናቀቁ ሥራዎች የሉም፡፡ በብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ የፍልሰት ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ለማካሄድ የሥራ ቡድን ራሱን ችሎ ተደራጅቶ

የነበረ ቢሆንም፣ በተለይም የምርመራ እና የጥናት እንዲሁም የማስተባበር ሥራዎችን በተመለከተ በተሟላ መልኩ በመፈጸም ረገድ ጉድለቶች መኖራቸውን መረዳት ተችሏል::[19]

### 3.2.3. የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የትምህርት ተደራሽነት እና ግንዛቤ ማሳደግ ሥራዎች

መንግሥት በሴቶች እና ሕፃናት የመነገድ ድርጊትን ተጨባጭ በሆነ መልኩ ለማስቀረት ኢኮኖሚያዊ እና ማኀበራዊ ባሕርይ ያላቸውን መንስዔዎች፣ ገፊ እና ሳቢ ምክኒያቶችን እና አጋላጭ ሁኔታዎችን ለመቀነስ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች መውሰድ አለበት:: ይህም የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር፣ ሴቶች መብታቸው፣ ክብራቸው እና ደኅንነታቸው ተጠብቆ እንዲሠሩ ማስቻል እና ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራትን እንዲሁም ሌሎች ማኅበራዊ መርኃ ግብሮችን ቀርጾ መተግበር ይጠበቅበታል:: በኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ ከገጠር ወደ ከተማ ለሚደረግ ፍልሰት በሳቢ ምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል የመሠረተ ልማት መስፋፋት፣ የትምህርት፣ የአገልግሎት ተደራሽነት እና ከሥራ ዕድሎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች መሆናቸውን የብሔራዊ የፍልሰት ፖሊሲው ያሳያል::

በከተማ እና በገጠር ያለውን የአገልግሎት ፍላጎት ለማጣጣም የሚጠቅሙ ሥራዎችን መንግሥት መሥራት ያለበት ቢሆንም፣ ኮሚሽኑ በክልሎች ከሚገኙ የሥራና ክህሎት ቢሮዎች ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ ላይ መሠረት በማድረግ በተገኘው መረጃ የተፈጠሩ የሥራ ዕድሎች በተለይም የዜጎችን ፍላጎት ከማሟላት አንጻር በቂ እና ተደራሽ እንዳልሆኑ ተገልጿል:: ክትትል በተደረገባቸው አንዳንድ ቦታዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር የኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራሞች በተለይ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተዘረጉ የሴፍቲ ኔት ፕሮግራሞች መኖራቸው ቢጠቀስም ተደራሽነታቸው አናሳ እና በቀጥታ በሴቶች እና ሕፃናት የመነገድ ድርጊትን መከላከል ያለሙ አይደሉም::

ክትትል በተደረገባቸው አብዛኞዎቹ አካባቢዎች በትምህርት ሥርዓቱ በሰዎች የመነገድን ድርጊትን ለመከላከል በተለየ ሁኔታ የሚሠራ ሥራ እንደሌለ የተገለጸ ሲሆን ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎችን የተመለከተ ሙሉ መረጃ ለማግኘት አልተቻለም::ተማሪዎች ትምህርት ሲያቋርጡ የሚያቋርጡበትም ምክንያት በዝርዝር የማይገለጹ መሆኑን ይልቁን ሀገር በመልቀቅ ምክንያት የሚል ጥቅል መረጃ ብቻ እንዳለ ከቀድሞው ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ትምህርት ቢሮ የተገኘው መረጃ ያሳያል:: በሌሎች አካባቢዎች በተለይም በሕፃናት የመነገድ ድርጊት በተስፋፋባቸው አካባቢዎች የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራምን፤ የተማሪዎች የመቅረት መጠንን ለመቀነስ እና በሰዎች የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል:: ይሁንና የተገለጹት የመረጃ አያያዝ ሥርዓቶች ክፍተት እና በጉዳዩ ላይ ዕቅዶ ያለመሥራት ክፍተት ይታያል::

ግንዛቤ ማሳደግን በተመለከተ በብሔራዊ የፍልሰት የትብብር ጥምርት ሥር በተቋቋመው የግንዛቤና የንቅናቄ የሥራ ቡድን የኅብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግና የባሕሪ ለውጥ በማምጣት መደበኛ ያልሆነ ፍልስትን ለመቀነስ ብሔራዊ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ አዘጋጅቶ በማጠናቀቅ ላይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል:: የሥራ ቡድኑ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በርካታ የግንዛቤ ሥራዎችን እንዳከናወነ ሪፖርት የተደረገ ሲሆን መንግሥታዊ ባልሆኑም ድርጅቶች የተለያዩ

---

[19] ብሔራዊ የትብብር ጥምረት የፍልሰት አስተዳደር የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ፤ (2013 – 2017 ዓ.ም.)

አደረጃጀቶችን በተለይም የትምህርት ቤት ክበባትን እና ማኅበራዊ አደረጃጀቶቸን በመጠቀም የግንዘቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንደሚሰጡ ተገልጿል፡፡ ክትትሉ በተደረገባቸው በአንዳንድ አካበቢዎች በሰዎች የመነገድ ድርጊትን አስመልክቶ ሥልጠና መሰጠቱን እንጂ የሥልጠና መመርያዎች ሥልጠናው በምን ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን እና ዓለም አቀፋዊ በሆነው በሰዎች የመነገድ ድርጊት ላይ ብቻ ያተኮሩ ስለመሆናቸው ተጨማሪ ክትትል እና ትኩረት የሚሻ ነው፡፡

## 3.3. በወንጀል ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የተወሰዱ እርምጃዎች

መንግሥት በሴቶች እና በሕፃናት የመነገድ ድርጊትን ለመቆጣጠር፣ አጥፊዎችን ለመያዝ፣ ለመክሰስ፣ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎች እና ተቋማዊ አሠራሮችን ማጠናከር ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ማኅበረሰቡ በሰው መነገድ ድርጊት ሊፈጸም መሆኑን ወይም መፈጸሙን የሚያመላክቱ መረጃዎች ሲያገኝ ለሕግ አስፈጻሚ አካለት ጥቆማ የሚያደርግበትን የጥቆማ ሥርዓት መዘርጋት፣ የሕግ አስፈጻሚ አካላት የወንጀል አፈጻጸሙን ለመለየት እና ለመመርመር የሚያስችል ሥልጠና በመስጠት ተገቢውን ዕውቀት እንዲጨብጡ ማድረግ እና እነዚህን ሥራዎች ለመሥራት የትብብር ማዕቀፍ እንዲዘረጋ ማመቻቸት አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የአጥፊዎችን ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እንዲያስችል በአዋጅ ቁጥር 1178/12 በሰው የመነገድ ተግባር፣ ዘዴዎችና ዓላማ ወንጀል መደረጉ አበረታች እርምጃ ነው፡፡

### 3.3.1. ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የፖሊስ እና የዐቃቤ ሕግ ተቋማዊ አሠራር

በሰው መነገድ፣ ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ማሻገር እና በሕገ ወጥ መንገድ ሰውን ለሥራ ወደ ውጪ መላክ ወንጀል ለመከላከል እና መቆጣጠር የተቋቋመው ብሔራዊ ምክር ቤት በሰው መነገድን በተመለከተ የወንጀል መከላከልና ማስከበር የሥራ ቡድን ቢኖርም ክትትል በተደረገባቸው ሁሉም የፖሊስ ተቋማት በተለይም በሴቶችና በሕፃናት የመነገድ ድርጊት ምርመራ ተብሎ ተለይቶ የተደራጀ መምሪያ/የሥራ ክፍል እና ልዩ ብቃት ያለው መርማሪ ፖሊስ የለም፡፡ በፌደራል ፖሊስ የተደራጀ የድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች ምርመራ የሥራ ክፍል ቢኖርም በሰው የመነገድ ድርጊትን የሚመለከተው የምርመራ ሥራ ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በልማዳዊ አሠራር የተሰጠ መሆኑን እና የሥራ ክፍሉ ድንበር ተሻጋሪ በሆኑ በሰዎች የመነገድ ድርጊቶች ላይ ብቻ ምርመራ እንደሚያካሄድ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለዚህም እንደ መነሻ ሆኖ የሚጠቀሰው ያለው ሥልጣን እና ኃላፊነት ግልጽ አለመሆኑ እንደሆነ ኮሚሽኑ ካነጋገራቸው ኃላፊዎች ለመገንዘብ ችሏል፡፡

### 3.3.2. የወንጀል ምርመራ እና ክስ አቀራረብ

ኮሚሽኑ ክትትል ባደረገባቸው አካባቢዎች በሀገር ውስጥ በሰው የመነገድ ድርጊት የሚሳተፉ ግለሰቦች ሕፃናትን በማሰማራት ገቢ ለማስገባት በዋናነት በሊስትሮ፣ በሽመናና በሚዛን በመሳሰሉት ሥራ ይሠማራሉ፡፡ ሴቶች እና ሕፃናት 'የሠራሁበት ደመወዝ አልተከፈለኝም' በሚል ለፖሊስ ሪፖርት እንደሚያደርጉ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ፖሊስም ገንዘባቸውን የማስመለስ ሥራዎችን ከመሥራት ባለፈ ድርጊቱ የተፈጸመው ከሰዎች መነገድ ጋር በተያያዘ ስለመሆኑ የማጣራት ሥራ መሠራቱን የሚያሳይ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ከአሠሪ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች

በተገኘው መረጃ መሠረትም ለሥራ ፍለጋ በመናኃሪያዎች አካባቢ የሚገኙ ሴቶችን በመውሰድ ከሀገር ውስጥ አሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ጋር በማገናኘት ከኤጀንሲዎቹ አምስት መቶ ብር የሚቀበሉ ሰዎች እንዳሉ ገልጸዋል። ይህን ሁኔታ ፖሊስ እንዲሁም የሴቶችና ሕፃናት ቢሮዎች እንደሚያውቁት ጭምር ያስረዳሉ። ይሁን እንጂ ፖሊስ እነዚህ ቦታዎች እና አካላት ላይ ድርጊቱ በሰው የመነገድ ወንጀልን ማሟላቱን ምርመራ በማድረግ እና በማጣራት ተጠርጣሪዎችን መያዙን የሚያሳዩ መረጃዎች የሉም። በዚህ ረገድ በወንጀል መከላከል ሥራ የቅንጅት ክፍተት እንዳለ ይጠቁማል። ከብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅም በሀገር ውስጥ የሚደረጉ በሰው በተለይም በሴቶችና በሕፃናት የሚፈጸሙ የመነገድ ድርጊቶችን እንደ ወንጀል ቆጥሮ በመመርመር እና በመክሰስ ረገድ ውስንነት እንዳለ እና በተለይም በክልል ደረጃ ባሉ ባለሙያዎች ወንጀሉን በመለየት ረገድ ውስንነት እንዳለ አሳውቀዋል።

ክትትል በተደረገባቸው የፖሊስ መምሪያዎች ምንም እንኳን በሀገር ውስጥ የሚደረጉ በሰዎች የመነገድ ድርጊቶች አመላካች የሆኑ ማስረጃዎች ቢኖሩም እነዚህን ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግ ምርምራ አለመደረጉን ይልቁንም መጨረሻ ላይ የተከሰተው የብዝበዛ ተግባር ወይም ጥቃት ላይ ማተኮር፣ በሂደቱ የተካሄዱትን በሰው የመነገድን ድርጊት የሚያቋቁሙ ዝርዝር ተግባራትን ለቅሞ ምርመራ በማድረግና በሰው የመነገድ ክስ በማቅረብ ረገድ ውስንነት መኖሩ ታይቷል። የብሔራዊ የትብብር ጥምርቱ በ2015 ዓመታዊ ሪፖርቱ ላይም ከወንጀል መከላከልና ሕግ ማስከበር አንጻር ለሀገር ውስጥ በሰው የመነገድ ድርጊት የተሰጠው ትኩረት አናሳ እንደሆነ ገልጿል። ይህም መንግሥት የተጣለበትን ክስ የመመስረት እና የአጥፊዎችን ተጠያቂነት የማረጋገጥ ኃላፊነት በተሟላ መልኩ እንዳይወጣ ያደርጋል።

### 3.3.3. የሕግ አስከባሪ አካላትን ዐቅም ለማጎልበት የተወሰዱ እርምጃዎች

በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ (ፍትሕ ሚኒስቴር) ለፌደራል ፖሊስ፣ዐቃቢያነ ሕግ እና ዳኞች የወንጀል መከላከልና ምርመራ ሥራዎችን እንዲሁም ምዘና እና ተያያዥ ለሆኑ ጉዳዮች የዐቅም ግንባታ ሥራ እንደሚሠራ ተደነግጓል። ሆኖም በፍትሕ ሚኒስቴር የተዘጋጀው የሥልጠና መመሪያ በሀገር ውስጥ የሚፈጸም በሰው መነገድ ላይ የሚያተኩር ይዘት የለውም። በፍትሕ ሚኒስቴር በሚሰጡ አንዳንድ ሥልጠናዎችም በሀገር ውስጥ መነገድ ላይ በቀጥታ ሥራው የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነው አለመምጣታቸው ግንዛቤን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ተግዳሮት መሆኑን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል። ክትትል በተደረገባቸው ክልሎች የሕግ አስከባሪ አካላት በሀገር ውስጥ ሰዎች የመነገድ ድርጊትን በተመለከተ የሥልጠናም ሆነ ሌሎች ግንዛቤን ማዳበሪያ መድረኮችን እንደማያገኙ ገለጸዋል።

### 3.3.4. የሀገር ውስጥ በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን የተመለከተ የመረጃ ሥርዓት

በሰው ለመነገድ ድርጊት ተጋላጭ ወይም ተጎጂ የሆኑ ሴቶችና ሕፃናት ሰብአዊ መብቶቻቸው ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ፣ እንዲጠበቁ እና እንዲሟሉ መንግሥት የተደራጀ፣ ትክክለኛ፣ የተሰባጠረ፣ ለአጠቃቀም ምቹ፣ ለማኅበረሰቡ እና ለባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ የሆነ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ሊኖረው ይገባል። በብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ የ2015 ዓመታዊ ሪፖርት መሠረት የመረጃ መቀባበያ ፕሮቶኮል እና የመግባቢያ ሰነድ ከሕግ እና ከተቋማት ኃላፊነት አንጻር ተቃኝቶ ተስተካክሎ ለፊርማ ዝግጁ ተደርጓል እንዲሁም በፍልሰት ዙሪያ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ

አገልግሎት መረጃ እንዲያሰባስብ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ለክትትሉ መረጃ እስከተሰበሰበት ድረስ ክትትል በተደረገባቸው ቦታዎች፣ በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን የተመለከቱ መረጃዎች፣ የመብት ጥሰቶችን ወይም ወንጀሎችን በዐይነትና መጠን፣ እንዲሁም ጠቅላላ በፍትሕ ሂደት ያሉትን ገጽታዎች በሚያሳይ መልኩ የተሰባጠረና የተደራጀ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በጥቅሉ የተገኙ መረጃዎችም በተለያዩ ተቋማት የተለያዩ መሆኑን፣ መረጃ የሚለዋወጡበት ሥርዓት ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣ መረጃ የሚደራጀውም ክስ በተመሠረተባቸው ወንጀሎች ብቻ መሆኑን እንዲሁም በሀገር ውስጥ የሚደረጉ በሰዎች በተለይም በሴቶችና በሕፃናት የመነገድ ድርጊትን አስመልክቶ መረጃ ለማግኘት አመቺ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ በመሆኑም በክትትሉ በሴቶች እና በሕፃናት የመነገድ ድርጊት ስርጭትን ለመረዳት፣ በመብቶች አጠባበቅና አፈጻጸም ረገድ ክፍተቶችን ለመለየት፣ የመብት ጥሰቶችን ለመከላከል እና ሥልታዊ የሆኑ የመፍትሔ አማራጮችን ለመጠቆም ዕንቅፋት የሚሆን ነው፡፡

## 3.4. የተጎጂዎች ጥበቃ እና መልሶ ማቋቋም ሥራዎች

መንግሥት በሴቶችና ሕፃናት የመነገድ ድርጊት ለተጎጂዎች የሚያደርገው ጥበቃና መልሶ የማቋቋም ሥራ ሰብአዊ መብቶችን ማእከል በማድረግ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በመቀናጀት ሊሠራ ይገባዋል፡፡ በዚህ ረገድ ኢሰመኮ ክትትል ባደረገባቸው ሁሉም አካባቢዎች ተጎጂዎች እንዲያገግሙ እና እንዲቀላቀሉ የሚያደርጉ የመንግሥት መዋቅሮች ባይኖሩም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በተፈጠረ የቅብብሎሽ ሥርዓት ለተጎጂዎች አገልግሎት ለመስጠት ወደ ተቋቋሙ ማእከላት በመላክ በትብብር እንደሚሠሩ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም የተጎጂዎች የጥበቃ እና የመልሶ መቋቋም ሥራዎች በሀገር ውስጥ በሰው መነገድ ተጎጂዎች የሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት ላይ ትኩረት ያደረጉ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ተጎጅዎች የሚደረግላቸው ድጋፍ እና ጥበቃ ፈቃዳቸውን መሠረት ያደረገ መሆኑን እና የሚያገኙት አገልግሎትም ለፍትሕ አካሉ በሚያደርጉት ትብብር ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ መሆኑን ካነጋገርናቸው ተጎጅዎች መገንዘብ የተቻለ ሲሆን ይኸውም በአወንታዊ እርምጃ የሚታይ ነው፡፡ ለተጎጂዎች የሚሰጠው አገልግሎት የምግብ፤ የሕክምና የሥነ ልቦና፣ የሕይወት ክህሎት እና የሙያ ሥልጠና እንዲሁም የፍርድ ቤት ቀጠሮዎችን እንዲከታተሉ ድጋፍ ማድረግን የሚያካትት መሆኑን ተስተውሏል፡፡ ሆኖም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተቋቋሙ ማእከላት አብዛኛዎቹ በክልል ከተሞች የሚገኙ በመሆናቸው እና የመንግሥት ማእከላት ባለመኖራቸው ደኅንነታቸውን አደጋ ላይ ለሚጥሉ ሁኔታዎች እንደሚዳረጉ ገልጸዋል፡፡ ለምሳሌም ፖሊሶች በርቀት ምክንያት ወደ ማእከላት መላክ የማይችሉበት አጋጣሚ ሲፈጠር ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመውሰድ ለተወሰነ ጊዜ እንደሚያስቀምጧቸው አንዳንድ ጊዜም ወደ እራሳቸው ቤት እንደሚወስዷቸው በዚህም ሳቢያ አንዳንድ ጊዜ ለተጨማሪ ጥቃት የሚዳረጉበት ሁኔታ መኖሩን በብዙ አካባቢዎች ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የፖሊስ አባለት ገልጸዋል፡፡

አብዛኞቹ ማእከላት ለሕፃናት ምቹ እንዳልሆኑ፣ በማእከሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችም የሕፃናትን ልዩ ፍላጎት በማሟላት እና የሕፃናቱን ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ረገድ ውስንነቶች አሉባቸው፡፡ ለምሳሌ ተጎጂ ሕፃናትን ወደ መጡበት ለመመለስ በሚል ምክንያት ለደላሎች አሳልፈው

ከሰጧቸው በኋላ በአከባቢያቸው ለሚኖሩ ሰዎች እንዲሁም ላዘዋወሩአቸው ቤተሰብ አባላት ዳግም እንደሚያጋልጧቸው ለመገንዘብ ተችሏል። እንዲሁም በሰው መነገድ ድርጊት ተጎጂ የሆኑ ሴቶች እና ሕጻናትን በአግባቡ በመለየት በፍላጎታቸው ላይ የተመሠረተ ድጋፍ እና አገልግሎት መስጠት ላይ ክፍተት እንዳለ ለመረዳት ተችሏል። በማእከላቱ የሚሰጡ የምግብ፣ የሕክምና እና የንጽሕና አገልግሎቶች መኖሩ እንደ አወንታዊ እርምጃ የሚወሰድ ሲሆን ፣ የፍርድ ቤት ጉዳያቸው እስኪጠናቀቅ ለወራት በማእከሉ የቆዩ ሕፃናት የመጡበትን እና ያሉበትን ከተማ አለማወቅ ችግር ታይቷል። የፍርድ ቤት ጉዳዮችን ክትትል የሚያደርጉ ተጎጅዎች በሚኖሩበት ጊዜ የወንጀሉ ፈጻሚዎች የተጎጂ ቤተሰቦችን በገንዘብ በመደለል ተጎጅዎች ላይ ጫና መፍጠር እንዲሁም የማእከላቱ ሠራተኞች ተጎጅዎችን እንዲያስወጡ ዛቻና ማስፈራራት የሚደርስባቸው መሆኑን ያነጋገርናቸው የማእከሉ ሠራተኞች የገለጹ ሲሆን ለዚህ ዐይነቱ ተግባርም ከፍትሕ አካሉ ይህ ነው የሚባል ምላሽ እንደማይሰጥ መረዳት ተችሏል።

ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የተጎጂዎች ማቆያ ማእከላት ከመንግሥት ጋር የቅብብሎሽ አሠራር የተዘረጋ ቢሆንም ከመንግሥት ተገቢውን ድጋፍ እንደማያገኙ ገልጸዋል። በተለይም ለተጎጂዎች ጊዜያዊ ማእከል ግንባታ የሚውል የቦታ ድጋፍ ባለማግኘታቸው ተጎጂዎችን ለመቀላቀል እና ለሌሎች ድጋፎች ሊውል የሚችልን ገንዘብ አላግባብ ለቤት ኪራይ የሚያወጡ መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘም ኮሚሽኑ ከዚህ በፊት ባደረገው ክትትል የአዲስ አበባ ሴቶችና ማኅበራዊ ቢሮ ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ተታለው፣ ተማለው እንዲሁም በጠለፋ ልመናን ጨምሮ በተለያዩ ሥራዎች ለመሠማራት ወደ አዲስ አበባ የመጡትን ሰዎች፤ ሕፃናትን ጨምሮ ወደ መጡበት ለመመለስ በሚል ከመንገድ ላይ በብዛት በማፈስ እና በትልልቅ አዳራሾች ውስጥ በማሰር ካለፈቃዳቸው እንዲመለሱ እንደሚደረግ ለማወቅ ተችሏል።

## 3.5. በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን በተመለከተ የትብብር ሥርዓትን መፍጠር

በሰው የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ለማድረግ እና ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል መንግሥት የትብብር ሥርዓት መዘርጋት ይጠበቅበታል። በዚህ ረገድ የብሔራዊ የትብብር ጥምረቱ ከክልሎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት እና የመንግሥት አካላት በተናጠል እና በትብብር የሚሠሯቸው ሥራዎች ወሳኝ ናቸው። በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 ከተቋቋመው ብሔራዊ የትብብር ጥምረት በተጨማሪ የሥራ ቡድኖችን ለማደራጀትና አባላትን፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 563/13 መሠረት ስድስት የሥራ ቡድኖች ተቋቁመዋል። እነዚህ ሁለት ሰነዶች የትብብር ጥምረቱና የሥራ ቡድኖቹ የሚኖራቸውን ግንኙነት ማስቀመጡ የተናበበ ሥራ ለመሥራት ያስችላል።

ኮሚሽኑ በክልሎች ባደረገው ክትትል በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ተጠሪ የሆነ ብሔራዊ አስተባባሪ ጥምረት በማቋቋም በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀጽ 35(5) የተቀመጠውን አቅጣጫ መነሻ በማድረግ ወደ ሥራ ለመግባት የተሞከረ መሆኑን ተመልክቷል። ይሁን እንጂ መዋቅሩን ለመመሥረት የረቀቀው ሕግ ክትትል በተደረገባቸው ቦታዎች ባሉ ሁሉም ምክር ቤቶች ያልጸደቀ በመሆኑ በበጀት እና ጽሕፈት ቤት በማደራጀት ሥራዎች ረገድ ተግዳሮቶች እንዳሉበት የትብብር ጥምረቱ አባል ተቋማት ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል።

የብሔራዊ ምክር ቤቱም ሆነ የትብብር ጥምረቱ ሲቋቋም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግሥት ተቋማትን ያጠቃለለ ቢሆንም ተጎጂዎችን በመደገፍ ጉልህ ሚና ያላቸውን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አባል አለመሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የትብብር ጥምረቱ በ2015 ዓ.ም. በጀት ዓመታዊ ሪፖርቱ እንደገልጸው የጥምረቱ አባል ተቋማት ተወካዮች በየጊዜው መቀያየራቸው፣ መመሪያው በሚያዘው መሠረት ውሳኔ መስጠት የሚችሉና ሥራ የሚመሩ ኃላፊዎች እንደማይመደቡ፣ ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ተወካዮች እንደሚመደቡ፣ በተቋማቸው ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት እንደማያስተባብሩ፣ ራሱን እንደቻል አንድ ሥራ እንደማይቆጥሩት እና የተጠያቂነት ሥርዓት አለመዘርጋቱ እንደተግዳሮት ተጠቀሷል፡፡

በሌላ በኩል የብሔራዊ የተጎጂዎች የቅብብሎሽ ሥርዓት ለመዘርጋት መመሪያ ቁጥር 562/13 የተዘጋጀ ቢሆንም የሥራ ቡድኖች አፈጻጸም ውጤታማ እና የተደራጀ ትብብር የመፍጠር ሂደቱ ላይ ተግዳሮት እንደፈጠረ ክትትሉ አመላክቷል፡፡ በትብብር ጥምርቱ የ2015 ዓ.ም. ዓመታዊ ሪፖርት መሠረት የሥራ ቡድን መሪ ተቋማት መሪነታቸውን በሚፈለገው ልክ እንደማይወጡ፣ በመመሪያው መሠረት የቡድን ስብሰባዎች አለመካሄዳቸው፣ መረጃ በአግባቡ እንደማይዙ፣ በዚህም ሀገራዊ ሪፖርቶችን ለማጠናቀር የመረጃ ክፍተት ማጋጠሙ እንደተግዳሮት ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ሪፖርቱ የቅብብሎሽ መግባቢያ ሰነዱ አለመፈረሙ እና ሁሉም የሥራ ቡድኖች በእኩል አለመንቀሳቀሳቸው እንደችግር አስቀምጦታል፡፡

## ክፍል አራት

## 4. ምክረ ሐሳብ

ሀ. ለሕግ አውጪ

- የፌደራል እና የክልል መንግሥታት ሕፃናት ወደ ከተሞች በመፍለስና በልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች በመሰማራት ለብዝበዛ የሚዳረጉበትን ሁኔታ ለመቀነስ መንግሥት የማኅበራዊ መከላከያ ፕሮግራሞችን በመንደፍ ተግባራዊ እንዲያደርግ፤
- በክልሎች ያሉ የትብብር ጥምረት መዋቅሮች አስፈላጊው በጀት እንዲመደብላቸው እና በትብብር ሥራዎች ላይ ያሉ ክፍተቶችን ለማስወገድ በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 በተቀመጠው መሠረት የክልል ምክር ቤቶች አግባብነት ያላቸውን ተቋማት ያቀፈ እና ተጠሪነቱ ለክልሉ ፕሬዝዳንት የሆነ ምክር ቤት በሕግ እንዲያቋቁሙ፤

ለ. ለሕግ አስከባሪና ፍትሕ አካላት

- በሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ወንጀል ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎችን በሕጉ አግባብ ተጠያቂነት እንዲኖር ማስቻል፤
- በፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ዳኞችና ዐቃቢያን ሕግ በሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ወንጀል ጉዳዮችን ክስ አመሰራረት፣ አያያዝና አስተዳደር ላይ ተከታታይ እና የሚመዘን የግንዛቤ ማስጨበጫና የዐቅም ግንባታ ሥራዎች እንዲሠሩ ማስቻል፤
- በሀገር ውስጥ በሰዎች መነገድ ላይ የሚደረጉ የምርመራና ክስ አመሠራረት ሥራዎች ድርጊቱን ተከትሎ በደረሱ ጥቃቶች ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን ድርጊቱን የሚያቋቁሙት ተግባራት መሟላታቸውን መርምሮ በማረጋገጥ በሀገር ውስጥ በሚደረጉ በሰዎች የመነገድ ድርጊቶች ላይ ክስ በመመሥረትና አጥፊዎችን ተጠያቂ በማድረግ ተጎጂዎች ካሳን ጨምሮ ውጤታማ መፍትሔ እንዲያገኙ ማደረግ፤
- ለሕግ አስከባሪ አካላት በሀገር ውስጥ የሚደረጉ በሰዎች የመነገድ ድርጊቶችን በተመለከተ የክስ አቀራረብ ላይ ያሉ ችግሮችን በጥናት ለይቶ ማስተካከያ ማደረግ፤
- ማኅበረሰቡ በሰው መነገድ ድርጊት ሊፈጸም መሆኑን ወይም መፈጸሙን የሚያመልክቱ መረጃዎች ሲያገኝ ለሕግ አስፈጻሚ አካላት ጥቆማ የሚያደርግበትን ተደራሽ የጥቆማ ሥርዓት መዘርጋት፤
- በማእከላት የፍርድ ቤት ጉዳዮችን ክትትል ለሚያደርጉ ተጎጅዎች የሕግ አስፈጻሚ አካላት ተገቢውን ጥበቃና ከለላ መስጠት፤
- ለሕግ አስከባሪ አካላት በሰዎች የመነገድ ድርጊትን በሚመለከት በተለይም በሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ድርጊት ላይ ትኩረት በማድረግ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ማዘጋጀት፤
- ፖሊስ በሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ድርጊትን በተለይም በሴቶችና በሕፃናት የመነገድ ድርጊትን መከታተል የሚያስችል ዐቅምን እንዲያጎለብት ፤

- የፍትሕ ሚኒስቴር እና የፌዴራል ፖሊስ፣ ከክልል ፍትሕ ቢሮዎች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካለት ጋር በመቀናጀት የሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ድርጊቶች መነሻዎችን፤ መዳረሻዎችን የሚያስከትላቸውን የመብት ጥሰቶች በሚያሳይ መልኩ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር መረጃዎች ለትንታኔ፣ ለሕግ እና ለፖሊሲ ማሻሻያዎች ግብአት ሊሰጡ በሚችል መልኩ የመረጃ ሥርዓት እንዲዘረጉ፤

ሐ. ለሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እና የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

- በሀገሪቱ ያሉ የሥራ ሁኔታዎችን በቅርበት በመከታተል በተለይም ሴቶችና ሕፃናት የመነገድ ድርጊት ሊፈጸሙባቸው የሚችሉ የሥራ ሁኔታዎችን መቆጣጠርና የሀገሪቱ የአሠሪና ሠራተኛ ሕጎች እንዲከበሩ በተለይም በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት መሠረታዊ የሥራ ላይ መብቶችንና ግዴታዎችን እንዲተገበሩ ማስቻል፤
- በሴቶች እና ሕፃናት የመነገድ ድርጊትን ለመከላከል ያለሙ የሥራ ዕድሎችን ከዜጎች ፍላጎት ጋር በተጣጣመና ተደራሽነታቸውን ባረጋገጠ መንገድ እንዲያከናውን ማድረግ፤

መ. ለሚመለከታቸው የፌደራል መንግሥት ተቋማት

- ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ሥምምነቶች መሠረት በሰው የመነገድን ድርጊትን በጋራ እና በተናጠል ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 ሥልጣን በተሰጣቸው ተቋማት የወጡ መመርያዎች፣ የሥራ ዕቅዶች፣ ማሠልጠኛ ማንዋሎች እንዲሁም የድርጊት መርኃ ግብሮች በሀገር ውስጥ በሰዎች የመነገድ ድርጊትን የተመለከቱ ጉዳዮችን ለይተው የሚያስቀምጡ እና ምላሽ የሚሰጡ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገርን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና ለመግታት የተቋቋመው እና ተጠሪነቱ ለምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር የሆነው ብሔራዊ ምክር ቤት፣ የትብብር ጥምረት ጽሕፈት ቤት እና በሥሩ የተዋቀሩ የሥራ ቡድኖች በሰው መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚወጡ ስትራቴጂዎች ዝርዝር ዕቅዶች እንዲሁም የድርጊት መርኃ ግብሮች በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድ ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ ፤
- ብሔራዊ ትብብር ጥምረቱ በሀገር ውስጥ በሴቶች እና በሕፃናት መነገድን ለመከላከል የሚያስችሉ መረጃዎችን በማሰባሰብና፣ በማጠናቀር፣ የድርጊቶቹን መንስዔዎች፣ ባሕርያት፣ ክብደት እና ውጤቶች የተመለከቱ ጥናቶችን እንዲሠራ፤ የጥናት ውጤትን መሠረት በማድረግ መነሻ እና ሳቢ ምክንያቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፤
- ድርጊቱን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠርና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችን ለመደገፍ ለተጎጂ ማእከላት ተገቢውን የበጀትና ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎችን ማድረግን ጨምሮ በቂ ሀብት በመንግሥት በጀት ውስጥ እንዲካተት እንዲያደርጉ፤
- በፌደራልና የክልል ተቋማት የተደራጀ፣ የተሰባጠረና ወጥ የመረጃ አስተዳደርና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲዘረጉ፤
- ሀገር ውስጥ በሴቶች እና በሕፃናት የመነገድ ድርጊቶች አባባሽ፣ መጋቢ ወይም ሳቢ የሆኑ ምክንያቶችን እና መንስዔዎችን ለመለየት እና በልየታው መሠረት እርምጃ ለመውሰድ

የሚያስችሉ ጥናቶች በትብብር ጥምረት ጽሕፈት ቤት ሥር በተቋቋመው የጥናት እና ምርምር ቡድን ተሠርቶ መረጃን መሠረት ያደረጉ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፤

- የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በሴቶች እና ሕፃናት መነገድ ድርጊትን ለመከላከል የሚረዱ የግንዛቤ ፈጠራ እና የባሕሪ ለውጥን ለማምጣት የሚያስችሉ ሥራዎችን እንዲሠሩ፤
- የፍትሕ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ቢሮ፣ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት፣ ወላጆች፣ የአካባቢ ተወካይ መሪዎች፣ የሃይማኖት አባቶችን ጨምሮ ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ ለባለግዴታ አካላት፣ ተደራሽ መደበኛና ቀጣይነት ያለው ሥርዓተ ጾታን እና የሕፃናት የእድገት ደረጃንና ልዩ ፍላጎትን ከግምት ያስገባ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን እንዲሰጡና ውጤታማነቱን በመገምገም እንዲያሻሽሉ፤
- በ2014 ዓ.ም. የረቀቀው ብሔራዊ የፍልሰት ፖሊሲ ከመጽደቁ በፊት የፖሊሲው ጭብጦች፣ የትኩረት ነጥቦች፣ ስትራቴጂዎች በሀገር ውስጥ በሴቶች እና ሕፃናት መነገድን በተመለከተ ግልጽ የፖሊሲ መመርያዎች እንዲያስቀምጡና በሀገር ውስጥ መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የመንግሥት አካላትን ሚና በግልጽ በሕግ እንዲያስቀምጡ፤
- የተጎጅዎች ብሔራዊ የቅብብሎሽ ሥርዓት በሀገር ውስጥ በሴቶች እና በሕፃናት የመነገድ ድርጊት ተጎጂዎችን በተመለከተ በምን ሥርዓት እንደሚመራ፣ የግዴታ ፈጻሚ አካላት ኃላፊነት ምን ምን እንደሆነ በግልጽ እንዲያስቀምጥና ወደ ሥራ እንዲገባ፤

ሠ. ለክልል መንግሥታት እና ተቋማት

- በሰው መነገድን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የትብብር ጥምረት ባልተቋቋመባቸው ክልሎች ለማቋቋም የተረቀቁ ደንቦች በክልል መንግሥታት እንዲጸድቁ፤
- የክልሎች የፍትሕ ጥናትና ምርምር ኢኒስቲትዩቶች የክልሎች ተጨባጭ ሁኔታን መሠረት በማድረግ በክልላቸው ውስጥ በሴቶች እና በሕፃናት የመነገድ ድርጊቶች አባባሽ፣ መጋቢ ወይም ሳቢ የሆኑ ምክንያቶችን እና መንስዔዎችን በጥናት መለየት እና በየክልሎቹ ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችል ምክረ ሐሳቦች እንዲያቀርቡ፤
- የተጎጅ ማእከላት ተደራሽ ባልሆነባቸው፤ እንደአስፈላጊነቱ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር፤ ክልሎች የተጎጂ ማእከላትን በማቋቋም ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ::

ረ. መንግሥታዊ ላልሆኑ የሲቪል ማኅበራትና የተራድኦ ተቋማት

- በሰው የመነገድ ድርጊት ተጎጂ ለሆኑ ሰዎች በተለይም ሴቶችና ሕፃናት የመጠለያ፣ የማኅበራዊ ሥነ ልቦና ድጋፍና አገልግሎት፣ የሕግ ምክር አገልግሎት እንዲሁም የሥራ ክህሎት ስልጠናን የመሳሰሉትን ያጠቃለለ ጠቅላላ ድጋፍና አገልግሎት መስጠት፤
- በሰው የመነገድ ድርጊትን ለመጠቆም የቀጥታ የስልክ አገልግሎት መስጠትና ከፍትሕ አካላት ጋር የማገናኘት ሥራ መሥራት፤
- በጉዳዩ ላይ ሰፊ የሆኑ ጥናታዊ ምርምሮችን በማድረግ በሰው የመነገድ ድርጊት በሀገሪቱ ያለውን ስርጭት፣ አሳሳቢነትና መጠን መረዳትና ለሚመለከታቸው አካላት የጥናቱን ውጤት በማካፈል የጉትጎታ ሥራዎችን መሥራት፣

- ማኅበረሰብ የማንቃትና በሰው የመነገድ ድርጊትን የመከላከል ፕሮግራሞችን ቀርጾ መተግበር፣